# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 096 ታኅሣሥ 6 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# «አፍሪካ ከእርዳታ ተሳቃ በፈጠራ ሥራዎች ሳይ እንድታተኩር አሜሪካ ትደግፋለች»

- አንቶኒ ብሊንከን

**ጀማል ታመነ**

ዋሽንግተን፡- አፍሪካ ከእርዳታ ተላቃ በአዳዲስ ሃሳቦችና ፈጠራዎች ላይ ተመስርታ ለማደግ በምታደርገው ጥረት አሜሪካ ድጋፏን አጠናክራ እንደምትቀጥል የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሴክሬታሪ አንቶኒ ብሊንከን ገለጹ።

ሴክሬታሪ አንቶኒ ብሊንከን ትናንት በዋሽንግተን ዲሲ የአፍሪካ የመሪዎች ጉባዔ የፈጠራ ባለሙያዎች መድረክ ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር፤ አፍሪካ የልጆቿን የፈጠራ አቅም ተጠቅማ ለመበልጸግ በምታደርገው ጉዞ የአሜሪካ ድጋፍ አይለያትም።

አፍሪካ በአሁኑ ጊዜ ከ60 በመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝቧ ከሃያ አምስት ዓመት እድሜ ያነሰ ነው፤ ይህ ደግሞ ለማደግ ትልቅ እድል የሚፈጥር ነው። በአፍሪካ እያደገ የመጣው የሕዝብ ቁጥር ለአህጉሪቷ ብሎም በቀሪው ዓለም የኢኮኖሚ እድገት እንዲመዘገብ ትልቅ አስተዋፅኦ እንደሚያበርክት እምነታቸው መሆኑን ብሊንከን በንግግራቸው አንስተዋል።

«አፍሪካ ከእርዳታ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# በአማራ ክልል በጦርነቱ የወደሙ አካባቢዎችን መልሶ ለመገንባት ርብርብ እየተደረገ ነው

- በክልሉ 292 ቢሊዮን ብር የሚገመት ቁሳዊ ውድመት ደርሷል
- ለመልሶ ማቋቋምና ግንባታው ድጋፍ እንዲደረግ ጥሪ ቀርቧል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የአማራ ክልል በጦርነቱ የወደሙ አካባቢዎችን መልሶ የመገንባት እና የማቋቋም ስራ በተቀናጀ መንገድ እየሰራ መሆኑን የክልሉ በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፈንድ ጽህፈት ቤት አስታወቀ። በክልሉ 292 ቢሊዮን ብር የሚገመት ቁሳዊ ውደመት ደርሷል፤ ለመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ስራው የአገር ውስጥና የውጭ ድርጅቶች አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉም ጥሪ ቀርቧል።

የክልሉ በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፈንድ ጽህፈት ቤት ስራ አስኪያጅ ዶክተር አባተ ጌታሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በስምንት ዞኖችና በሁለት የከተማ አስተዳደሮች በመጀመሪያውና ሁለተኛው ዙር ወረራ ብቻ 292 ቢሊዮን ብር ቁሳዊ ውድመት ደርሷል። ከዚህ በላይ በገንዘብ ሊተመን የማይችል የከፋ የሰብአዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ማህበረ ባህላዊ ውድመቶች ተከስተዋል።

የአማራ ክልል በጦርነት ውድመት የደረሰባቸው አካባቢዎች መልሶ ለመገንባት ጽህፈት ቤት አቋቁሞ እየሰራ ነው ያሉት ዶክተር አባተ፤ በቀጣይ አምስት ዓመት የሚተገበር ስትራቴጂክ እቅድ ባለፈው ሀምሌ ወር 2014 ዓ.ም በቦርድ ጽድቆ ወደ ስራ ተገብቷል ብለዋል። እቅዱ በዋናነት የጤና፣ ትምህርት፣ ግብርናን ጨምሮ በ18 ዋና መስሪያ ቤቶች ጋር በመቀናጀት የተነደፈ ነው። ከዕቅዱ በ2015 በጀት ዓመት

በአማራ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










ፎቶ - አዩብ ተፈሪ

## በትግራይ ክልል በሚቀጥሉት አምስት ወራት ትምህርት ሙሉ ለሙሉ ይጀመራል

ገጽ 4






WORLD BANK

## የዓለም ባንክ በኢትዮጵያ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ ለተጎዱ ዜጎች የሚውል 745 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ አደረገ

ገጽ 4

# ኢንስቲትዩቱ የአየር ሁኔታው በሰብል ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለመቀነስ ቅድመ ዝግጅት እንዲደረግ አሳሰበ

**ሄርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በሚቀጥሉት ቀናት ደረቅና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በሰብል ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለመቀነስ አርሶ አደሮች ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስትቲዩት አሳሰበ።

የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስትቲዩት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ከታኅሰሳ 2፣ 2015 ዓ.ም ጀምሮ በተያዘውና ለተከታታይ 10 ቀናት በሚቀጥለው የአየር ሁኔታ ትንበያ ደረቅና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ይኖራል።

ይህ መሆኑ በመከናወን ላይ ለሚገኘው ሰብል ስብሰባ እና ድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ በጎ ጎን የሚኖረው ቢሆንም እድገታቸውን ባልጨረሱ እና በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ ፍራፍሬ ተክሎች እና የጓሮ አትክልቶች ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል።

በመሆኑም አርሶ አደሮች ቀጣዩ የአየር ሁኔታ እድገታቸውን ባልጨረሱ እና በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ ፍራፍሬ ተክሎች እና የጓሮ አትክልቶች የሚደርሰውን ተፅዕኖ ለመቀነስ እንደ አካባቢው ሁኔታ የሚኖረውን ቅዝቃዜ ለማሻሻል የሚረዱ ተግባራትን ለማከናወን ዘግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ከታህሳስ ሁለት 2015 ዓ.ም የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ፤ ከአውሮፓ ወደ ሀገራችን የሚገባ ደረቅና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚጎላበት ጊዜ እንደሆነ በመግለፅ፤ በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሌሊቱ እና የማለዳው ቅዝቃዜ አንፃራዊ ጥንካሬ ሊያሳይ ይችላል ሲል ሪፖርቱ ይጠቁማል።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ደረቃማው የአየር ሁኔታ በብዙ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ቀጣይነት የሚኖረው እንደሆነና ከዚሁም ጋር ተያይዞ በተለይ በደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠነክር እንደሚችል የትንበያ መረጃው ያሳያል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የለሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከዕለት ወደ ዕለት በአንዳንድ ቦታዎች መጨመሩን በመግለፅ በተለይ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች የቅዝቃዜው መጠን ከ 5 ዲግሪ ሴልሽስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል ያለው መግለጫው፤ ደብረብርሃን፣ ሐሮማያ፣ ዳንግላ እና ሌሎች ስፍራዎች እንደ አብነት ጠቅሷል።

በሌላ በኩል በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብ ኦሮሚያና የደቡብ ሱማሌ አካባቢዎች ከነበራቸው የደመና ሽፋን በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ዝናብ ማግኘታቸውን በመግለፅ፤ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል ጋምቤላ፣ ጂንካ እና ሳውላ ይገኙበታል ብሏል።

እንደ ኢንስትቲዩቱ ገለፃ፤ ባለፉት አስር ቀናት የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በኢሉአባቡራ፣ በባስኬቶ፣ በሞያሌ እንዲሁም በቆራሄ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው። የተቀሩት አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል ሲል ገልጿል።

ኢንስቲትዩቱ በመግለጫው የአየር ንብረቱ በእርሻ ስራ ላይ ያሳደረው አወንታዊ ተፅእኖ እንደነበረ በመጠቆም፤ የበጋው ደረቅ አየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለ ነበር ብሏል። ይህም ሁኔታ መኸር አብቃይ በሆኑት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ በመካሄድ ላይ ላለው ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል ብሏል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ከከባድ እስከ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ማግኘታቸውን ተከትሎ፤ በተለያየ የእድገት ደረጃ ለሚገኙ የበጋ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተሻለ የግጦሽ ሳር እና የመጠጥ ውሃ እንዲኖራቸው ያስቻለ እንደነበር አትቷል።

ኢንስትቱዩቱ የአየር ሁኔታው በውሃ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅእኖ እንደገለፀው፤ በአብዛኛው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ አመዝኖ እንደነበር በመግለፅ፤ በመካከለኛ እና በታችኛው አሞ ጊቤ፣ በላይኛው እና መካከለኛው ባሮአኮቦ እንዲሁም በጥቂት ታችኛው ስምጥ ሸለቆ እና በገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸው ብሏል።

በተጨማሪም በጥቂት መካከለኛው አሞ ጊቤ እና የላይኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች በአብዛኛው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ነበራቸው ሲል አክሏል።

# የከተማዋን የውሃ ችግር ለመፍታት በአንድ ቢሊዮን ብር አምስት የውሃ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ ነው

**ሞገስ ተስፋ**



አቶ ሲሬ ጀማል

ሆሳዕና፡- የከተማዋን የውሃ ችግር ለመፍታት በአንድ ቢሊዮን ብር በጀት አምስት የውሃ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ መሆኑን የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር አስታወቀ። በ420 ሚሊዮን ብር 14 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር የውስጥ ለውስጥ መንገድ ማስፋፊያም እየተሰራ ነው።

የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ሲሬ ጀማል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቀደም ሲል በነበረው ሥርዓት የሀብት ፍትሃዊ አጠቃቀም አልነበረም። በዚህም ከተጎዱ አካባቢዎች አንዱ የሀድያ ዞንና አካባቢው ነው። በዚህ የተነሳ በሆሳዕና ከተማ ምንም አይነት የመሰረተ ልማት ፍሰት አልነበረም። ከለውጡ ወዲህ ግን በርካታ ስራዎች እየተከናወኑ ነው።

እንደ አቶ ሲሬ ገለጻ፤ የከተማዋ አንዱ ችግር የሆነው የውስጥ ለውስጥ የአስፓልት መንገድ በሁለት ምዕራፍ እየገነባ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ 14 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር የውስጥ ለውስጥ አስፓልት መንገድ በከተማ አስተዳደሩና በሕዝብ ተሳትፎ እየተገነባ ነው። አሁን ላይ ሦስት ኪሎ ሜትር የሚሆነው የመንገድ ግንባታ አስፓልት የማንጠፍ ስራ እየተሰራ ሲሆን ሌላኛው 5 ኪሎ ሜትር የሚደርሰውን መንገድ ግንባታ ለማስጀመር በሂደት ላይ ነው። ፒስታ የሆኑ መንገዶችን ወደ አስፓልት ደረጃ የማሳደግ ስራም ይከናወናል ብለዋል ከንቲባው።

ከተወሰኑ አካባቢዎች ውጭ የከተማዋ ነዋሪዎች ውሃ የሚያገኙት በ15 ቀን አንድ ጊዜ ነው። ሆቴሎች ደንበኞቻቸውን ተቀብለው ለማስተናገድ ባለው የውሃ እጥረት ምክንያት እንደሚቸገሩ የገለጹት ከንቲባው፤ የከተማዋን የውሃ ችግር ለመቅረፍ አምስት የሚደርሱ የከርሰ ምድር የውሃ ጉድጓዶች እየተቆፈሩ ነው። ሲጠናቀቁ የከተማዋን የውሃ ፍላጎት ሙሉ ለሙሉ የሚቀርፍ ነው።

ከአምስቱ ውስጥ ሁለቱ ተጠናቀው ወደ ከተማ የማስገባት ስራ እየተሰራ ነው። ሁለቱ ጉድጓዶች በሰከንድ 120 ሊትር ውሃ ያስገኛሉ፤ ፕሮጀክቱም በመጠናቀቅ ላይ ነው። መጠባበቂያ ማጠራቀሚያ የተጠናቀቁ ሲሆን ታህሳስ 30 አካባቢ አገልግሎት ይሰጣሉ። በከተማዋ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ የቱሪስት መዳረሻ የሆነችው የሆሳዕና ከተማን በሚፈለገው ደረጃ ማድረስ ይቻላል ሲሉ አቶ ሲሬ ገልጸዋል።

14 ነጥብ 5 ኪሎሜትር መንገድ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ማስፋፊያ 420 ሚሊዮን በላይ ብር በጀት እየተሰራ ነው ያሉት ከንቲባው፤ እስካሁን ድረስ አንድ መቶ ሃያ ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል ብለዋል።

በአጠቃላይ ለአምስት የውሃ ፕሮጀክቶች በአንድ ቢሊዮን ብር በጀት ለመገንባት እቅድ የተያዘ ሲሆን ለሁለት የውሃ ፕሮጀክቶቹ ማጠቃለያ 165 ሚሊዮን ብር ወጪ መደረጉን ተናግረዋል።

በከተማዋ የተጀመሩ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ለማጠናቀቅ የሕዝብ ተሳትፎ ንቅናቄ እንደሚደረግም አቶ ሲሬ ገልጸዋል።



# የማር ምርትን የሚያሳድጉ ከ50 ሺህ በላይ የዕፅዋት ችግኞች ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ሆነዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው ዓመት ብቻ ለማር ምርት አስተዋፅኦ ያላቸው ከ50 ሺህ በላይ የተለያዩ የዕፅዋት ችግኞች ለአርሶ አደሩ ተደራሽ መደረጋቸውን የሆለታ የንብ ምርምር ማዕከል ገለጸ።

የሆለታ ንብ ምርምር ማዕከል ከፍተኛ ተመራማሪና ብሔራዊ የንብ ምርምር አስተባባሪ ዶክተር አምሳሉ በዛብህ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የማር ምርትን ማሻሻል የሚያስችል ሙሉ ፓኬጅ ተቀርፆ ስራ ተጀምሯል። በዘንድሮው ዓመት ብቻ ለማር ምርት አስተዋፅኦ ያላቸው ከ50 ሺህ በላይ የተለያዩ የዕፅዋት ችግኞች ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ተደርገዋል።

የማር ምርትን አይነትና ጥራት የሚወስኑ ከ2 ሺህ በላይ የዕፅዋት ዝርያዎች ተለይተው ለተጠቃሚው እንዲደርሱ እየተደረገ መሆኑንም ጠቁመው፤ የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብሩ ዋና ዓላማ የተመጣጠነ የአመጋገብ ሥርዓት መፍጠር መሆኑን ተናግረዋል።

የንብ ውጤቶችን በማዕድ ውስጥ ማካተት የአመጋገብ ሥርዓታችንን ያሻሽላል ያሉት ዶክተር አምሳሉ፤ የተመጣጠነ ምግብ የመጠን አቅርቦት ብቻ ባለመሆኑ በጥራት የሚቀርብ ማር በምግብ እጥረት ምክንያት የሚመጣውን የመቀንጨር ችግር ሊከላከል ይችላል ብለዋል።

በሌማት ትሩፋት የተያዘውን ግብ ለማሳካት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የማር ምርት ለማግኘት የሚያስችል የንብ ብዜትና ዘመናዊ የንብ ቀፎ ለህብረተሰቡ እያቀረበ መሆኑን የገለጹት ደግሞ የሆለታ የንብ ምርምር ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ከበበው ዋቅጅራ፤ በኢትዮጵያ ያለውን ዕምቅ ሀብት በምርምር በመደገፍ የሌማት ትሩፋት ግቦችን ቀድሞ ማሳካት እንደሚቻል ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ከአንድ የንብ ቀፎ በዓመት የሚያገኙት የማር ምርት ከ10 ኪሎ ግራም የማይበልጥ መሆኑን ጠቅሰው ምርቱን ለማሻሻል የተለያዩ ስራዎች በመከናወን ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆለታ ንብ ምርምር ማዕከል በምርምር እስከ 60 ኪሎ ግራም ማር ማምረት የሚያስችል የዘር ብዜትና የቴክኖሎጂ አቅርቦት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ተጀምሯል ብለዋል።

በሆለታ ንብ ምርምር ማዕከል የተሻለ ምርት የሚሰጡ አምስት ንዑስ የንብ ዝርያዎች እንዳሉ በጥናት ማረጋገጡንም ተናግረዋል።

ከተለያዩ ዕጽዋት ከዘጠኝ በላይ የማር አይነቶችን ማምረት የሚቻል መሆኑን ገልጸው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመራጭና ልዩ የሆነ ከአንድ አይነት ዕጽዋት የሚገኝ የቡና፣ የግራዋ፣ የባህር ዛፍን ጨምሮ ዘጠኝ አይነት ማር ማምረት ጀምረናል ብለዋል። በዚህም ኢትዮጵያ በማር ምርት የሌማት ትሩፋት ግቧን ቀድማ ማሳካት የሚያስችላት በምርምር የተደገፈ የንብ ማነብ ቴክኖሎጂና የማር ምርት ማግኘት ትችላለች ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በዓመት ማምረት ከምትችለው 500 ሺህ ቶን ማር አንጻር ሲታይ በሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር የተያዘውን ዕቅድ ማሳካት የሚያስችል አቅም አለን ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚያደርጋት ከአስር ሚሊዮን በላይ የንብ መንጋ እንዳላት ቢነገርም በዓመት የምታገኘው የማር ምርት ግን ከ70 ሺህ ቶን አይበልጥም።

የኢትዮጵያን የንብ ሀብት በተመለከተ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በአገሪቷ ካለው 10 ሚሊዮን የንብ መንጋ ሰባት ሚሊዮኑ በአርሶ አደሮች ዘንድ ሲገኝ 3 ሚሊየኑ ደግሞ በጫካ የተበተነ መሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ዜና

# በሰሜን ወሎ ዞን 18 ሺህ የሚጠጉ ሰዎች በወባ በሽታ ተይዘዋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን በወባ በሽታ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 17 ሺህ 988 መድረሱን የዞኑ ጤና መምሪያ አስታወቀ።

የሰሜን ወሎ ዞን ጤና መምሪያ ሃላፊ ሲስተር ፈለቁ መኮንን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት፤ በዞኑ ለወባ መራቢያ ምቹ የሆኑ ቦታዎች በጦርነት ቀጠና ውስጥ በመቆየታቸው ምክንያት የቅድመ መከላከል ሥራ ሳይሠራ ቆይቷል፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ የወባ ሥርጭት ሊጨምር ችሏል።

በሁሉም ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች ላይ 59 ሺህ 671 የህብረተሰብ ክፍሎች የወባ በሽታ ምርመራ እንደተደረገላቸው የተናገሩት ኃላፊዋ፤ ከተመረመሩት ውስጥ በ17 ሺህ 988 ሰዎች ላይ የወባ በሽታ እንደተገኘባቸው ገልጸዋል።

የሰሜን ወሎ ዞን በክረምት ወቅት የጦርነት ቀጠና ውስጥ የነበረ በመሆኑ የተለያዩ የቅድመ መከላከል ስራዎች እንዳልተሰሩ የጠቆሙት ሃላፊዋ በዚህም የተነሳ በዞኑ ቆላማ አካባቢዎች የወባ በሽታ ስርጭት በከፍተኛ መጠን እንደጨመረ አንስተዋል። የዞኑ አብዛኛዎቹ አካባቢዎች ለወባ መራቢያ ምቹ ሲሆኑ በስምንት ወረዳዎች እና ከተሞች በወባ በሽታ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር ከባለፈው ጊዜያት እየጨመረ እንደመጣ ገልጸዋል።

በዞኑ የተከሰተውን ከፍተኛ የሆነ የወባ በሽታ ስርጭት የመመርመር እና የመለየት ሥራ በጤና ተቋማቱ እየተከናወነ መሆኑን እና በቂ ግብአት እንዳላቸውም አክለው ተናግረዋል።

የወባ በሽታን ለመከላከል የህክምና አገልግሎት ብቻ መስጠት በቂ እንዳልሆነ ያነሱት ሃላፊዋ ቋሚ የወባ መራቢያ ቦታዎችን በመለየት የቁጥጥር ስራ መስራት እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል። በመሆኑም የታቆሩ ውሃዎችን ማፋሰስ እና ጊዜያዊ የወባ መራቢያ ቦታዎችንም በመለየት ህብረተሰቡን ያሳተፈ ስራ በመስራት ላይ እንደሚገኙ አብራርተዋል።

በዞኑ ባለፉት ጊዜያት የወባ በሽታ ስርጭትን መቀነስ ተችሎ የነበረ ቢሆንም በተከሰተው ጦርነት ምክንያት በርካታ የጤና ተቋማት በመውደማቸው እና የቅድመ መከላከል ስራ ባለመሰራቱ ችግሩ እንደ አዲስ እንዲባባስ አድርጎታል ብለዋል።



ሲስተር ፈለቁ መኮንን

በሽታውን ለመቆጣጠር ህብረተሰቡ በወባ መከላከል እና ማስወገድ ላይ ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ፣ የወባ ትንኝ ቁጥጥር ስራዎችን ማጠናከር፣ ህብረተሰቡ አጎበሮችን እንዲጠቀም ማድረግ፣ የወባ በሽታ ህክምና አገልግሎት መስጠት እና ሌሎች ተያያዥ ስራዎችን መስራት ከጤና ተቋማት እና ከማኅበረሰቡ የሚጠበቅ ተግባር ነው ሲሉ ሲስተር ፈለቁ አክለዋል።

በሌላ በኩል የሕክምና ተቋማቱ በሦስተኛው ዙር የሀገሪቱ የሰሜኑ ክፍል ጦርነት በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት ለኅብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት በሚችሉበት አቅም ላይ አለመሆናቸውን አስረድተው፤ ተቋማቱ አገልግሎት እንዲሰጡ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜም ሁሉም የጤና ተቋማት ባለሙያ ተሟልቶላቸው ለአገልግሎት ክፍት የተደረጉ ቢሆንም የላብራቶሪ አገልግሎት፣ ማህበረሰቡ የሚፈልገውን አይነት ህክምና እና የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት እየሰጡ እንዳልሆነ ሃላፊዋ አንስተዋል።

# የትግራይ ሕዝብ ፍላጎት ስምምነቱ ተግባራዊ ሆኖ ሰላም እንዲሰፍን ነው

**መአርግ ገ/እግዚአብሔር**

አዲስ አበባ፡- በአሁኑ ጊዜ የትግራይ ሕዝብ ፍላጎት በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሆኖ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ነው ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) ምክትል ሊቀመንበር አቶ መስፍን ደሳለኝ ተናገሩ።

አቶ መስፍን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ የትግራይ ሕዝብ ሰላምን አጥብቆ ይፈልጋል። በሁለቱም አካላት የተደረሰው የሰላም ስምምነት በፍጥነት ወደ መሬት ወርዶ አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን ይሻል።

የትግራይ ሕዝብ ከተጋረጠበት ችግር ለመውጣት ሙሉ ሰላሙ እንዲመለስለት ይፈልጋል ያሉት ምክትል ሊቀመንበሩ፤ ይሁን እንጂ የሰላም ስምምነቱን ለማደናቀፍ የሚሞክሩ አካላት ስላሉ እነዚህን ጸረ ሰላም ሃይሎች ሕዝቡ ከመንግሥት ጎን በመቆም ሊታገላቸው ይገባል ብለዋል።

እነዚህ አካላት የትግራይ ሕዝብ እስካሁን የከፈለው መስዋዕትነት ይበቃዋል፣ ሰላም ያስፈልገዋል ማለት ሲገባቸው የተደረሰው የሰላም ስምምነት ተግባራዊ እንዳይሆን እንቅፋት ለመፍጠር መሞከር ተገቢ እንዳልሆነ የጠቀሱት አቶ መስፍን፤ በተለይም በስሜት ተነስተው የሰላሙን ስምምነት እያጣጣሉ ያሉ የትግራይ ዳያስፖራዎች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ጠይቀዋል።



አቶ መስፍን ደሳለኝ

የትግራይ ሕዝብ በጦርነት ብቻ ሳይሆን በመድሃኒት፣ የምግብ እና ሌሎች መሰረታዊ ፍላጎቶች እጦት ችግር ለመላቀቅ ጥረት እየተደረገበት ባለበት በአሁኑ ወቅት ጦርነቱን እንደገና ለማስቀጠል የሰላም ስምምነቱን ማደፍረስ መሞከር ሕዝቡን እንደገና ለችግርና ለእልቂት መጋበዝ መሆኑን አመልክተዋል።

ሰላም ፈላጊው ሕዝብ ጸረ- ሰላም ሃይሎችን አጥብቆ መታገል አለበት ያሉት ምክትል ሊቀመንበሩ፤ የትግራይ ሕዝብም በጦርነት ችግር ይፈታል ብለው የሚያምኑትን የገዛ ወገኑን ወደ ሰላማዊ ሁኔታ መመለስ እንደሚጠበቅበትና ጦርነት ፈላጊዎቹም ቢሆን ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለሕዝቡ ማሰብ አለባቸው ብለዋል።

እንደ አቶ መስፍን ማብራሪያ፣ ከሰላም ይልቅ ጦርነትን የሚቀሰቅሱ ወገኖች ለትግራይን ሕዝብ አስበው ሳይሆን ለራሳቸው ትርፍ ሲሉ ነው። በተለይ የትግራይ ዲያስፖራዎች ለራሳቸው ሰላም ባለበት አገር ሆኖ ጦርነት መቀስቀስ የለባቸውም። የትግራይ ሕዝብ የሚፈልገው ጦርነት ሳይሆን ሰላም መሆኑን ደጋግሞ እየተናገረ ነው።

ጦርነት የሚያስከትለውን መዘዝ ከትግራይ ሕዝብ በላይ የሚያውቀው የለም ያሉት አቶ መስፍን፤ የትግራይ ሕዝብ ሰላም ነው የምንፈልገው እያለ ባለበት በአሁኑ ጊዜ፣ የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ለማደፍረስ መሞከር ከሰብአዊ ፍጡር የማይጠበቅ ተግባር ነው ብለዋል።

የተደረሰው የሰላም ስምምነት ለትግራይ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያውያን ጠቃሚ መሆኑን ገልጸው፤ ስምምነቱ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሆኖ ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ሁሉም የሚመለከተው አካል አወንታዊ አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት ሲሉ አሳስበዋል።

# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከ11 ሺህ በላይ ሰራተኞችን ሊቀጥር ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከ 11 ሺህ በላይ አዳዲስ ሰራተኞችን ለመቅጠር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር እየሰራ መሆኑን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባዘጋጀው የአዲስ ሰራተኞች ቅጥር ላይ በተለያዩ ማህበራዊ ድረ ገጾች ሲነሱ የነበሩ ቅሬታዎችን አስመልክቶ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋራ በጋራ በመሆን በትናንትናው እለት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል።

የባንኩ የሰው ሃይል አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ኤፍሬም መኩሪያ በማህበራዊ ትስስር ገጾች ፈተናው ወጥቷል ተብሎ ሲሰራጭ የነበረው መረጃ ከእውነት የራቀ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ኤፍሬም ገለጻ ባንኩ የሰራተኞች ቅጥር ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጎ እየሰራ ሲሆን በዚህ ረገድ የቅጥር ሂደቱ ተአማኒ እንዲሆን የጽሁፍ ፈተናውን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የንግድ ክፍል እንዲያዘጋጅ መደረጉን ተናግረዋል።

የዘንድሮ የጀማሪ የባንክ ባለሙያዎች የጽሁፍ ፈተና እንዳይሰረቅ ውስን ሰዎች እንዲሳተፉበትና በኮድ በማዘጋጀት አስፈላጊው ጥንቃቄ መደረጉንም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በባንኩ ኢንዱስትሪ ውስጥ ከፍተኛ የሰው ሃይል በመቅጠር እና በማብቃት የመሪነት ሚና እየተጫወተ ያለ ተቋም ነው ያሉት አቶ ኤፍሬም፤ ላለፉት 80 ዓመታት ጀማሪ የባንክ ባለሙያዎች እና ተለማማጅ ማኔጅመንቶችን የማብቃት ስራ ሲከውን መቆየቱን ጠቁመዋል። በአሁኑ ጊዜም ከ 70ሺ በላይ ቋሚና ጊዜያዊ ሰራተኞች እንዳሉት ታውቋል።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ወክለው ንግግር ያደረጉት ዶክተር አብራራው ጫኔ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው ለረጅም ዓመታት በፈተና አወጣጥ ላይ ልምድ ያካበተ ተቋም እንደመሆኑ ፈተናው እንዳይሰረቅ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረጉን ገልጸው ፈተናውን እንዲያዘጋጁ የተመረጡት መምህራንም ዩኒቨርሲቲውን ከ30 ዓመታት በላይ በእኔነት ስሜት ያገለገሉ ናቸው ብለዋል።

ባንኩ ባወጣው የቅጥር ማስታወቂያ ከ130 ሺህ በላይ ስራ ፈላጊዎች ያመለከቱ ሲሆን ዝቅተኛውን መስፈርት ያሟሉ ሁሉም አመልካቾች የጽሁፍ ፈተና እንዲወስዱ መደረጉም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአገሪቱ የተለያዩ ከተሞች ላይ ከ30 በላይ ዲስትሪክቶች እና ከ 1800 በላይ ቅርንጫፎች እንዳሉት ይታወቃል።

# የዓለም ባንክ በኢትዮጵያ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ ለተጎዱ ዜጎች የሚውል 745 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ አደረገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-የዓለም ባንክ በኢትዮጵያ በሰው ሰራሽና ተፈጥሮ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች አገልግሎት የሚውል የ 745 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ አደረገ።

የኢትዮጵያ፣ የኤርትራ፣ የደቡብ ሱዳን እና የሱዳን የዓለም ባንክ ቡድን ዳይሬክተር ኦስማን ዲዮን እንደገለጹት ባንኩ በኢትዮጵያ ለተሻለ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት እና በጎርፍ የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ለማድረግ 745 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ አድርጓል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በኮቪድ-19፣ ከአየር ንብረት ጋር በተያያዙ አደጋዎች እና አስከፊ ግጭቶችን ጨምሮ በተለያዩ ቀውሶች ተጎድተዋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ እነዚህ ቀውሶች የጤና አገልግሎቶችን አቅርቦት በከፍተኛ ደረጃ በማስተጓጎል ኢትዮጵያ ባለፉት አስርት ዓመታት ያስመዘገበችውን የጤና ውጤት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ግስጋሴ እንዲቀንስ ማድረጉን ጠቁመዋል። ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎችም ወደ 24 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች በቂ የጤና አገልግሎት አያገኙም ሲሉ አክለዋል።

ከዚህም ባሻገር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ የጎርፍ ክስተቶች በድግግሞሽ እና በመጠን በከፍተኛ ሁኔታ ጨምረዋል። እ.ኤ.አ. በ2020 ብቻ በጎርፍ አደጋ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን ተጎድተዋል፣ ወደ 300 ሺህ የሚጠጉት ተፈናቅለዋል እንዲሁም 288 ሰዎች ለሞት ተዳርገዋል ብለዋል።

የዓለም ባንክ በቅርቡ ባደረገው ግምገማ በ2020 የጎርፍ አደጋ ኢትዮጵያ ወደ 358 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ንብረት፣ መሰረተ ልማት እና የሰብል መሬት ላይ ጉዳት አድርሷል። የጎርፍ አደጋ በእርሻ እና በከብት እርባታ ላይ ያስከተለው ተጽእኖ ቀድሞውንም የነበረውን አሳሳቢ የሰብአዊ ሁኔታ አባብሶታል። አፋጣኝ መፍትሄ ካልተሰጠ በስተቀር እነዚህ ለውጦች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገትን ሊያዳክሙ ይችላሉ።

የዓለም ባንክ የኢትዮጵያውያንን መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት እና ለአቅመ ደካሞች መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ በሰዎች ላይ ያተኮረ አካሄድ ይከተላል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በዚህ መሰረት የባንኩ የስራ አስፈፃሚ ቦርድ ለኢትዮጵያ ፕሮጀክቶችን ማጽደቁን ይፋ አድርገዋል።

አንደኛው የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አገልግሎትን ለማጠናከር ከዓለም አቀፍ ልማት ማህበር (IDA) በተገኘ የ400 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ እና ከግሎባል ፋይናንሺንግ ተቋም (ጂኤፍኤፍ) በተገኘ የ45 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ አስፈላጊ እና ፍትሃዊ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ለማሻሻል ያለመ ነው ብለዋል።

ቁልፍ የሥነ-ተዋልዶ፣ የእናቶችና ሕፃናት ጤና እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎት ለመስጠት ያለመ ሲሆን በግጭት የተጎዱ አካባቢዎችን ጨምሮ በተለይም ለሴቶችና ሕጻናት የሚውል ነው። ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች በሶስተኛ ወገን ፈጻሚ ኤጀንሲ አማካይነት ወደ እነዚህ ቦታዎች የመግባት ሂደት እንደሚከናወንም አስታውቋል።

“የጤና ፕሮጀክቱ በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች እና ተፈናቃዮችን ጨምሮ ከ22 ሚሊዮን በላይ ሴቶች እና ሕጻናት ሕይወት አድን የጤና አገልግሎቶችን እንደ ክትባት፣ የቤተሰብ ምጣኔ፣ የሰለጠነ የወሊድ፣ የቅድመ ወሊድ እና የድህረ ወሊድ አገልግሎት ይሰጣል። በተጨማሪም በግጭት የተጎዱ ሕንጻዎች ወደነበሩበት እንዲመለሱ በማድረግ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የሚያስፈልጋቸውን አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል ብለዋል።

ከዓለም አቀፍ ልማት ማህበር በተገኘ የ300 ሚሊዮን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ የተደረገው የጎርፍ አደጋ አስተዳደር ፕሮጀክት ኢትዮጵያ ከአየር ንብረት ጋር በተያያዙ የሚያጋጥሙ አደጋዎችን የመቋቋም አቅሟን በአፋጣኝ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ያለመ ነው።

በ1960 የተቋቋመው የዓለም ባንክ ዓለም አቀፍ ልማት ማህበር (አይዲኤ) የኢኮኖሚ እድገትን ለሚጨምሩ፣ ድህነትን ለሚቀንሱ እና የድሆችን ሕይወት የሚያሻሽሉ ፕሮጀክቶችን እና ፕሮግራሞችን በእርዳታ እና ከዜሮ እስከ ዜሮ ወለድ ብድር በመስጠት ለዓለም ድሃ ሀገራት ይረዳል።

# በአማራ ክልል...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የሚሰሩትን ለይቶ መሬት የወረደ ስራ እየተሰራ ነው ብለዋል።

ከሁሉም መስሪያ ቤቶች አንድ አንድ ተወካይ ያሉበት የዓመት እቅድ ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን የገለጹት ዋና ስራ አስኪያጁ፤ ባለፈው ህዳር 23 በክልሉ ፕሬዚዳንት መሪነት የ2015 የመጀመሪያ የመልሶ ማቋቋም ስራ በሰሜን ወሎ ወርቄ ቀበሌ ላይ ተጀምሯል ብለዋል።

ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች መልሶ ማቋቋም የሚቻለው ሁሉም ሰው በአቅሙ ሲደጋገፍና ሲረዳዳ ነው። በሰሜን ወሎ ዞን ወርቄና ያያ የሚባሉ ሁለት ቀበሌዎች ላይ 234 የሚደርሱ ቤቶች፣ አንድ ጤና ጣቢያ፣ አንድ ትምህርት ቤት፣ ሙሉ በሙሉ የወደመባቸው ናቸው። የወደሙ 234 ቤቶችን በማስገንባት መልሶ ማቋቋምና ግንባታው መጀመሩን አስታውሰዋል።

በጦርነቱ ስምንት ዞኖችንና ሁለት የከተማ አስተዳደሮችን ጨምሮ መልሶ ለማቋቋም እንቅስቃሴ መጀመሩን የገለጹት ዶክተር አባተ፤ የሁሉም የዞንና የከተማ አመራሮችና የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች የተሳተፉበት ስራ ተከናውኗል ሲሉም ጠቅሰዋል።

በቀጣይም እያንዳንዱ ተወካይ በቀበሌ ደረጃ ወርዶ ሀብት ማሰባሰብ እንዳለበት አቅጣጫ ተቀምጧል ብለዋል።

የመልሶ ማቋቋምና ግንባታው የክልሉ መንግሥት በመደበው አንድ ቢሊዮን ብር በጀት መጀመሩንም ስራ አስኪያጁ ጠቁመዋል። መልሶ ግንባታ ስራው በሰሜን ጎንደር፣ ደቡብ ጎንደር፣ ዋግኽምራ፣ ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ፤ ደሴ ከተማ፣ ኮምቦልቻ ከተማ፣ ኦሮሞ በሔረሰብ ዞንና ሰሜን ሸዋ የሚተገበር ነው።

እንደ ዶክተር አባተ ገለጻ፤ ሙሉ በሙሉ የወደሙ ትምህርት ቤቶች አንድ ሺ 151 ናቸው። ከነዚህ ውስጥ በትምህርት ሚኒስቴር 45 ትምህርት ቤቶች፣ በክልሉ 22 ትምህርት ቤቶች እየገነቡ ነው። በጤና ተቋማት 10 ክሊኒክ፣ አንድ ሆስፒታል፣ በግብርና፣ የተለያዩ የእንስሳት ክሊኒኮች፣ ግብርና ኮሌጆች፣ 64 የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን፣ 17 የወጣት የሥነምግባር ማጎልበቻ ማዕከላት፣ በሁሉም ዞኖች የሚገኙ ሲሆን እነዚህን ማዕከል ያደረገ የመልሶ ግንባታ ስራ እየተከናወነ ነው።

በተጨማሪም 10 የስራ ዕድል ፈጠራ ማዕከል የአንድ ማዕከል አገልግሎት የሚሰጡ እያንዳንዳቸው አንድ ሺ ሰው የሚገለገልበት ማዕል መልሶ ግንባታ፣ በውሃ 31 የሚሆኑ የተለያዩ ጉድጓዶችን፣ ምንጮችን የመገንባት፣ 421 ሄክታር መሬት ሊያለማ የሚችል የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ለመገንባት ኮንትራክተሮች ውል ወስደው በሁሉም ዞኖች በመሄድ ስራ እንዲጀምሩ ተደርጓል። ለዚህም አንድ ቢሊዮን አንድ መቶ 29 ሚሊዮን ብር ተመድቦ እየተከናወነ ስለመሆኑ ገልጸዋል።

ዶክተር አባተ፣ ውድመቱ ከባድ ነው፣ የሚፈልገው ድጋፍ ከፍተኛ ነው። ከክልሉ ጋር የዓለም ባንክ ዩኤንዲፒ፣ ወርልድ ቪዥን ከክልሉ መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ጽህፈት ቤት በጋራ በቅንጅት እየሰሩ ነው። 53 የሚሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተለይተው በተናበበ መንገድ እየተሰራ ነው። ሀብትን በትክክል በመጠቀም የመልሶ ግንባታና ማቋቋም ስራው ውጤታማ እንዲሆን የሁሉም ኃላፊነት ነው። ለዚህ ስራ ስኬታማነት የአገር ውስጥ ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ ግብረሰናይ ድርጅቶችና መላ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ እንዲያደርጉ ዶክተር አባተ ጥሪ አቅርበዋል።

# «አፍሪካ ከእርዳታ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በ2016 እ.ኤ.አ በአፍሪካ የሚገኙ የቢዝነስ ፈጠራ ሃሳብ አመንጪዎች ከ350 ሚሊዮን ዶላር ያልበለጠ የኢንቨስትመንት እድገት እንዳስመዘገቡ አንስተው፤ ይህ ቁጥር ባለፈው ዓመት አድጎ ከአምስት ቢሊዮን ዶላር በላይ በኢንቨስትመንት ዘርፍ ገቢ እንዲመዘገብ ማስቻላቸውንም አንስተዋል።

አፍሪካ ያላትን የወጣቶች ሀብት ተጠቅማ እንድትበለጽግ አሜሪካ የምታደርገውን ዘርፈ ብዙ ድጋፍ አጠናክራ ትቀጥላለች ያሉት ሴክሪታሪ ብሊንከን፤ አሜሪካ ይህን የምታደርገው አፍሪካውያን የቢዝነስ ፈጠራ ባለሙያዎች ከአህጉሪቱ ባለፈ ለአሜሪካ ብሎም ለመላው ዓለም የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው ብለዋል።

‹‹አፍሪካ እርዳታ ሳይሆን ፈጠራን ትሻለች›› ይህ እንዲሳካ አሜሪካ በአፍሪካ የፈጠራ ሃሳቦች እንዲያድጉ በሶስት መንገዶች ድጋፍ እንደምታደርግ አንስተዋል።

አሜሪካ በአፍሪካ ለሚከናወኑ የፈጠራ ስራዎች እንዲጠናከሩ መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉ ታደርጋለች፣ ወጣት መሪዎች አቅማቸው እንዲጎለብት የሚያስችል ተግባራትን ታከናውናለች እንዲሁም አሜሪካውያን ካምፓኒዎች በአፍሪካ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲያሳድጉ የሀገሪቱ መንግሥት ጥረት ያደርጋል ብለዋል።

በአፍሪካውያን የቢዝነስ ፈጠራ ሃሳብ ባላቸው ዜጎች የተመረቱ ምርቶች በአሜሪካ ገበያ እየቀረቡ መሆኑን የገለጹት ሴክሬታሪ ብሊንከን፤ ይህ ተጠናክሮ እንደሚጥልም አስረድተዋል።

በአሜሪካ ዋሽንግተን ትናንት በጀመረው የአሜሪካ አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ የተለያዩ የጎንዮሽ ውይይቶች ተካሂደውበታል።

የአፍሪካውያንና ዲያስፖራ ወጣት መሪዎች ፎረም፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፎረም፣ የአፍሪካ ከቀረጥ ነጻ የንግድ ሚኒስትሮች ሰብሰባ፣ የአሜሪካ አፍሪካ ስፔስ ፎረም፣ ሰላም፣ ደህንነትና አስተዳደር ፎረም፣ ቀጣይነት ያለው የጤና ትብብር ፎረም እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ ላይ ትኩረት ያደረጉ ውይይቶች ተካሂደዋል።

በመድረኩ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ጨምሮ የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች እየተሳተፉ ነው።

ጉባዔው በሁለተኛ ቀን ውሎው በአሜሪካና አፍሪካ የቢዝነስና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የሚመክር ይሆናል።

# በትግራይ ክልል በሚቀጥሉት አምስት ወራት ትምህርት ሙሉ ለሙሉ ይጀመራል

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል ለሁለት ዓመታት ያህል ተቋርጦ የነበረውን የመማር ማስተማር ሂደት በቀጣዮቹ አምስት ወራት ሙሉ ለሙሉ ለማስጀመር እየተሰራ መሆኑን የትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት መሰረተ ልማትና አገልግሎቶች ዴስክ ኃላፊ አቶ ዳዊት አዘነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ጦርነት የተካሄደባቸው አካባቢዎች የትምህርት መቋረጥ ችግር ቢታይም በትግራይ ክልል ደግሞ ላለፉት ሁለት ዓመታት ትምህርት ተቋርጦ ቆይቷል።

በነበረው ጦርነት ምክንያት የትምህርት መዋቅሩ ጭምር የፈረሰ በመሆኑ መረጃዎችን እንኳን ለመለዋወጥ አስቸጋሪ ሁኔታን መፍጠሩን የተናገሩት አቶ ዳዊት፤ ሆኖም የትምህርት ሥራ የሚቋረጥ አይደለምና ከዘርፉ ጋር የሚሰሩ አካላትን በመጠቀም የትምህርት ሥራውን ለማስጀመር የሚያስችሉ ተግባራትን ለማከናወን እቅዶች መያዛቸውንና በሚቀጥሉት አምስት ወራትም ሙሉ በሙሉ በክልሉ ትምህርት ለማስጀመር ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ ዳዊት፤ በክልሉ የትምህርት ቢሮዎች ጭምር የፈረሱ በመሆናቸው የሰው ሀብት የማደራጀት፣ የፈረሱ ትምህርት ቤቶችን የመጠገንና ግብዓት የማሟላት ተግባራት እንደሚከናወኑ ገልጸው፤ በጦርነቱ ምክንያት የወደሙትንና እድሳት የሚደረግላቸውን በመለየት በመረጃው መሰረት ለመማር ማስተማሩ ምቹ ይደረጋሉም ብለዋል።

እንደ አቶ ዳዊት ማብራሪያ፤ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ግብዓት አቅርቦት ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ተብሎ የተለየ ነው። ቅድሚያ ግን የሥርዓተ ትምህርት ክለሳ ይደረጋል። ምክንያቱም ተማሪዎች በጦርነቱ ምክንያት መማር ባለመቻላቸው የመጡ በርካታ ችግሮች አሉ። ስለሆነም ያሉበትን ክፍል በደንብ አውቀውበት ወደቀጣዩ ክፍል እንዲዛወሩ ለማስቻል የሚረዳ ሥርዓት ይዘረጋል።

በተጨማሪም በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት መሰረት ተማሪዎች መማር የሚችሉበት ሁኔታ ላይ ዝግጅት እንደሚደረግ ያነሱት ኃላፊው፤ ከግብዓት አቅርቦት አንጻርም መጽሐፍትን ማዘጋጀትና አባዝቶ የማቅረብ ተግባራት እንደሚከናወኑ አስገንዝበዋል።

በትግራይ ክልል የመማር ማስተማር ሥራው ሲጀመርም ከሌሎች ክልሎች በተለየ መልኩ እንደሆነ የጠቆሙት አቶ ዳዊት፤ ተማሪዎች፣ መምህራንና ወላጆች አእምሯቸውን የሚያነቃቁ ተግባራትና ድባብ የሚፈጥሩ ነገሮች ከትምህርት ቅበላው ጀምሮ እንደሚከናወንላቸው ጠቁመዋል።

የቅድመ ዝግጅት ንቅናቄም እንዲሁ በስፋት እንደሚከናወንና ከዚህ ጎን ለጎንም ተማሪዎችን፣ መምህራንንና አመራሩን የሥነልቦና ዝግጅት እንዲያደርጉ የማስቻል ተግባር ይከናወናል ሲሉም አብራርተዋል።

በአፋርና በአማራ በመጠኑም ቢሆን እየተደረገ ያለው የተማሪዎች ምገባ ስራ በትግራይም የብዙዎችን እገዛ የሚፈልግ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ዳዊት፤ በትግራይ የተማሪዎችን ምገባ ለማስጀመር አጋር አካላት፤ በውጭ የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ጦርነቱ ያልደረሰባቸው አካባቢዎች ላይ የሚኖሩ ተወላጆች ድጋፍ እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል።

በክልሉ ያለውን ውስብስብ ችግር ለመፍታት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ የተካሄደው የሰላም ስምምነቱ መልካም አጋጣሚዎችን እንደፈጠረ የሚያነሱት አቶ ዳዊት፤ መልካም አጋጣሚውን ተጠቅሞ የመማር ማስተማር ሥራውን ሊያሳልጡ የሚችሉ ተግባራትን ለማከናወን የተለዩ የትኩረት አቅጣጫዎች መቀመጣቸውን ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሰላም ስምምነቱ ተፈጻሚነት ቁርጠኝነትንና ተግባራዊ እርምጃን ይጠይቃል!

መንግስት ከሕወሓት ጋር ያጋጠመውን አለመግባባት ገና ከጅምሩ በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለመፍታት ረጅም ርቀት መሄዱ ይታወሳል ። የአገር ሽማግሌዎችን ጨምሮ እናቶችን ወደ መቀሌ በመላክ አለመግባባቶች ወደ ግጭት እንዳያመሩ ሰፊ ጥረት አድርጓል።

አለመግባባቶች ወደ ግጭት ከተለወጡና ወደ ጦርነት ከተገባ በኋላም ቢሆን ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት በተለያዩ ወቅቶች ስለ ሰላም ጥሪዎችን ከማቅረብ ጀምሮ፤ የተናጠል የተኩስ አቁም በማድረግ በተግባር አሳይቷል። በዚህም ያልተገቡ ዋጋዎችን ለመክፈል ተገድዷል።

ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ለድርድር ራሱን በማዘጋጀት ወደ ድርድር በመግባትም ፤በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተደረገው የሰላም ስምምነት እውን እንዲሆን በግንባር ቀደምትነት ተንቀሳቅሷል፤ አሁን ለተደረሰበት ሰላምና ሰላሙ እየፈጠረ ላለው አገራዊ እፎይታም ትልቅ አቅም መሆን ችሏል።

መንግስት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ለጀመረው አገራዊ የለውጥ ጉዞ እና ራዕይ አድርጎ ለተነሳለት ብልጽግና ሰላም ዋነኛ ጉዳይ መሆኑን በስፋት መክሯል፤ በተግባርም እስከ ፕሪቶሪያው ስምምነት ድረስ በቁርጠኝነት ተንቀሳቅሷል።

ከስምምነቱ በኋላም በስምምነቱ የተቀመጡ ውሳኔዎችን በማክበር ለተፈጻሚነታቸው በስፋት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። የጠላትነት መንፈስን ከሚፈጥሩና ከሚያባብሱ ጉዳዮች ከመቆጠብ ጀምሮ ከግጭት ፈጣሪና አባባሽ ችግሮች ራሱን ቆጥቦ እየተንቀሳቀሰ ነው። የሽግግር ፍትህ ተግባራዊ እንዲሆንም እየሰራ ነው።

የሰብአዊ ርዳታ አቅርቦቶች ያለገደብ ወደ ትግራይ ክልል የሚገቡበትን አሰራር በመፍጠር የክልሉ ህዝብ አቅርቦቶቹን በስፋት እንዲያገኝ እያደረገም ነው። ከኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ወደ ክልሉ 98 ሺ 92 ነጥብ 16 ሜትሪክ ቶን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ የዕርዳታ ቁሳቁስ እንዲሁም 690ሺ 868 ሊትር ነዳጅ ማጓጓዝ ተችሏል።

በመንግሥት በኩል 13 ሺህ 686 ነጥብ ስምንት ሜትሪክ ቶን የተጓጓዘ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥም አንድ ሺ 222 ነጥብ 76 ሜትሪክ ቶን መድኃኒት፣ ሰባት ሺህ 651 ሜትሪክ ቶን ምግብ ነክ ያልሆኑ እርዳታዎች፣ 690 ሺህ 868 ሊትር ነዳጅ ነው። ሰብዓዊ ድጋፎቹን ለማድረስም 2 ሺ398 ተሽከርካሪዎች ተሰማርተዋል። ይህንንም በማድረግ ከአምስት ሚሊዮን በላይ ህዝብ ተጠቃሚ ሆኗል።

ይህ መንግስት የርዳታ አቅርቦቶች ወደ ክልሉ በስፋት እንዲገቡ ያለውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ ያሳየ ሲሆን፤ ወደ ክልሉ ከገባው የእርዳታ አቅርቦት ውስጥም መንግስት ከ13ሺ ሜትሪክ ቶን በላይ በራሱ ለማቅረብ የሄደበት ርቀት በክልሉ ለሚገኙ ዜጎች ያለውን አጋርነት በተጨባጭ ያሳየ ነው።

ከዚህም ባለፈ በጦርነቱ የወደሙ መሰረታዊ አገልግሎቶችን/የመብራትና የስልክ...ወዘተ/በርካታ የሰው ኃይል በመመደብ በዘመቻ ወደ ስራ እንዲገቡ እያደረገ ያለው ጥረትና እየተመዘገበ ያለው ውጤትም ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ ያለውን ቁርጠኝነት ያመላከተ ነው።

መቀሌን ጨምሮ ሽሬን የመሳሰሉ የክልሉ ከተሞች የመብራት አገልግሎት እንዲያገኙ የተደረገበት መንገድም ሆነ፤ አሁንም ሌሎች የክልሉ አካባቢዎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል እየተደረገ ያለው የተቀናጀ ጥረት የዚሁ የመንግስት ቁርጠኝነት ማሳያ ነው።

ይህ የመንግስት ቁርጠኝነት በብዙ መልኩ የሚበረታታና ዓለም አቀፍ እውቅና ያተረፈ ቢሆንም፤ አጠቃላይ ለሆነው የሰላም ስምምነቱ ተፈጻሚነት፤ በሕወሓት በኩል ተመሳሳይ ቁርጠኝነት መፍጠርና በተግባር ማሳየት የሚጠበቅ ይሆናል።

ሕወሓት በአደባባይ እንደሚናገረውና የሰላም ስምምነቱ ለትግራይ ህዝብ ካለው ሁለንተናዊ ጠቀሜታ አንጻር፤ በስምምነቱ ላይ የተቀመጡ ውሳኔዎችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተግባራዊ እንዲሆኑ ከፍ ባለ ቁርጠኝነት ሊንቀሳቀስ ይገባል።

እንደ አገርና ሕዝብ ትናንት ብዙ ዋጋ ካስከፈለን ጦርነት ወጥተን በስምምነቱ ማጣጣም የጀመርነውን ሰላም ዘላቂ ለማድረግ ለስምምነቱ ታማኝ ከመሆን ውጪ ሌላ አማራጭ የለም። ለዚህ ደግሞ ራስን ለተግባር ማስገዛት ወሳኝ ይሆናል!


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


### ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ሌብነትና ሌቦች ላይ የተጀመረው እርምጃው ተጠናክሮ እንዲቀጥል...

**ሜሎዲ ከኳስ ሜዳ**

ኢትዮጵያ ውስጥ ሙብት በገንዘብ የሚገዛበት ደረጃ ላይ ተደርሷል:: ሕዝብ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከመሬት ጋር በተያያዙ አሠራሮች፣ በፋይናንስ ዘርፍ፣ በሸያጭና ግዥ ሂደቶችና በፍትሕ አደባባዮች ቅሬታ እያሰማ ነው ። ችግሩ ከዕለት እለት እየተባባሰ እንጂ ሲሻሻል አይታይም።

ለዚህም ከሙስና ወንጀል ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጠንከር ያሉ ሕጎች ቢኖሩም አተገባበራቸው በመላላቱ፣ በሙስና የተሳተፉ አካላትን የማጋለጥና በሕግ የመጠየቅ ሁኔታ እምብዛም መሆኑ እንደምክንያት ይነሳል:: ለዚህም መንግስትን ጨምሮ መላው ሕዝብ ተጠያቂ ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ።

በርግጥ ስለ ሙስናና ሊያስከትል ስለሚችለው አገራዊ አደጋ ብዙ ቢወራም፤ ችግሩን መዋጋት የሚችል ተቋም ተቋቁሞ ወደ ስራ ቢገባም፤ ለችግሩ በመንግስት ደረጃ የተሰጠው ትኩረት የችግሩን ያህል ባለመሆኑ ዛሬም ሙስና አገራዊ አጀንዳ ሆኗል።

አሁን ላይ ችግሩ የደረሰበት ደረጃም የከፋ ስለመሆኑም ዜጎች በእለት ተእለት ሕይወታቸው እየታዘቡት ያለ ተጨባጭ እውነታ ከሆነ ውሎ አድሯል። ይህን ጉዳይ ለመገንዘብ ወደ አንድ መንግስታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ጎራ ማለት በራሱ በቂ ነው::

የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ወደ ስልጣን ከመጡበት ማግስት ጀምሮ ሙስናን አምርሮ መታገል እንደሚገባ በተደጋጋሚ በአደባባይ ሲናገሩ ተደምጠዋል::

‹‹ሙስና ዛሬ የአገራችን የደኅንነት ሥጋት ሆኗል:: ወደ ብልጽግና የምናደርገውን ጉዞ እጅ ተወርች አሥሮ ለመያዝ ከጠላቶቻችን እኩል ሙሰኛው እየታገለን ነው:: ሕዝባችን በአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከመሬት ጋር በተያያዙ አሠራሮች፣ በፋይናንስ ዘርፍ፣ በሸያጭና ግዥ ሂደቶች፣ በፍትሕ አደባባዮች፣ በተለያዩ የመንግስት ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች፣ የህዝብ ተቋማት ወዘተ. በሚያጋጥመው ሙስና እየተማረረ ነው:: ...ከጸጥታ ሥጋቶች እኩል ሙስና የብልጽግና ጉዟችን ዋናው ዕንቅፋት ሆኗል›› ሲሉም ተናግረዋል::

ችግሩን አምርሮ መታገል እንደሚገባ ሲያሳስቡ የቆየት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሰሞኑን ደግሞ ችግሩን በዘመቻ መዋጋት የሚያስችል ስትራቴጂ ነድፈው ሰባት አባላትን ያቀፈ ብሔራዊ የፀረ ሙስና ኮሚቴ መቋቋሙንም ይፋ አድርገው ስራ አስጀምረዋል::

መንግሥት የችግሩን አሳሳቢነት ተረድቶ ኮሚቴ ማቋቋሙ፣ በየደረጃው ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በተመሳሳይ ኮሚቴ ማቋቋማቸው ይበል ያሰኛል:: በውሳኔው ማግስት የተጀመሩ ርምጃዎችም ይበረታታሉ። ነገር ግን ሥር የሰደደውን የሙስና ችግር በዚህ ብቻ ሊፈታ እንደማይችል ይታመናል::

መንግሥት ባለፉት ዓመታት በጦርነት፣ በኮቪድ ወረርሽኝና መሰል የቤት ስራዎች በመጠመዱ ትኩረቱን ወቅታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማተኮሩን ተከትሎ/ምክንያት በማድረግ ችግሩ ተስፋፍቶ፣ ሕጋዊ የሚመስል ስሪት ተበጅቶለት ታይቷል:: ሌቦችም አገራዊ ችግሮችን እንደመልካም አጋጣሚ ተጠቅመውበታል። ይህን ችግሩን ለማስወገድ ለሚደረገው ትግል "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ " ሆኖበታል።

በርግጥ በነዚህም አገራዊ አስቻጋሪ ወቅቶች ሙስናን መታገል የሚያስችሉ ጥረቶች የሉም ማለት አልነበረም፤ ጥረቶች ተደርገዋል። ውጤታቸው ግን እንዲህ ነው ተብሎ አፍ ሞልቶ መናገር የሚያስችል አይደለም።

ለምሳሌ የአደጋ ስጋትና ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር ከሙስና ጋር በተያያዘ ተጠያቂ ሆነው ጉዳያቸውን በፍርድ ቤት እየተከታተሉ ናቸው:: ችግሩ ግን አንድን አመራር ፍርድ ቤት በማቅረብ እና ተጠያቂ በማድረግ የሚፈታ አይደለም።

በተቀናጀና ዘላቂነት ባለው መልኩ ከፍ ባለ ቁርጠኝነት ሊተገበር የሚገባ ነው፤ ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ከመድፈን ጀምሮ፤ ሙሰኞችን ለፍርድ በማቅረብ እና ለጥፋታቸው ተመጣጣኝና አስተማሪ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። ለሙስና የበለጠ ተጋላጭ ናቸው የሚባሉ ተቋማት ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል።

ከሁሉም በላይ የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣትና ትርጉም ያለው ውጤት ለማምጣት እንዲችል የኅብረተሰቡ ሙሉ ትብብር ወሳኝና እጅግ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

ሌቦችን የሚያጋልጡ ሰዎችን በመሸለም እና ከለላ በመስጠት ማበረታታት አስፈላጊ ነው:: ማኅበረሰቡ የሚጨበጥ ነገር ማየት ስለሚፈልግ መሬት ላይ የሚታይ ርምጃ እየወሰዱ ሕዝብ በመንግሥት ርምጃ መተማመን እንዲኖረው ማድረግ ይገባል።

በርግጥ የሙስና ወንጀል በሚስጥርና በጥንቃቄ የሚፈጸም ወንጀል እንደመሆኑ ስርቆት መፈጸሙን ለማወቅ የሚያስችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አይቻልም:: ድርጊቱ በድብቅ እና በሚስጥር ከመፈጸሙ ባሻገርም አጥፊው ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል አሻራ የማጥፋት አቅም ስላለውም ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል::

የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል:: በአንጻሩ ደግሞ በአገርና በህዝብ ላይ የሚያሳርፈው ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነው:: ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆንም ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ብሎ ጉዳዩን ለህግ የሚጠቁም፣ አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና አጥፊዎች እንዲቀጡ የሚያደርግ ሰው ላይገኝ ይችላል:: በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ እጅግ ብዙ ነው::

ከዚህ አንጻር ዜጎች ስለሙስና በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በስፋት መስራት ያስፈልጋል። የሙስና ወንጀል አገርን አደጋ ውስጥ በመክተት ትውልድ ተሻጋሪ ችግር ምንጭ ሊሆን እንደሚችል ተረድቶ ሊዋጋው የሚችልበትን የአይምሮ ዝግጁነት መፍጠር ወሳኝ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥታዊ ሌብነት/ሙስና ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩን እየቀያየረና በጣም ተቋማዊ በሚመስል ደረጃ ጎልብቶና የአገር ህልውና ስጋት ሆኖ ይታያል:: ግለሰቦች ተጠያቂነትን ባለመፍራት ጭምር በአደባባይ የሚያደርጉት ነገር እየሆነ መጥቷል።

ለውጡ እንዲመጣ አንዱ ምክንያት ሕዝቡ በመንግሥታዊ ሌብነት እጅግ በመማረሩና ያንን ለማስወገድ በተደረገ ትግል እንደነበር ማንም የሚዘነጋው አይመስለኝም:: በተለይም በሕዝባዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማለትም እንደመሬት አስተዳደርና ገቢዎች አካባቢ የነበረው ችግር ማንሳት ይቻላል:: ይህ ደግሞ የሕብረተሰቡን አቅም በመፈታተኑ መንግሥት ላይ ያለው እምነት ተሸርሽሮ ወደ ተቃውሞ ማምራቱን መንገር ለቀባሪው ማርዳት ይሆናል::

ችግሩ አሁን ላይ በመንግሥታዊ መዋቅር ስር የሰደደ ሆኗል:: የሌብነት ሰንሰለት ተዘርግቶለት በከፍተኛ አመራሮች ጭምር እየተሠራ መሆኑ ችግሩን ለመቅጨት አዳጋች ሊያደርገው እንደሚችል መገመት ይቻላል። በሙስና ላይ የሚደረገው ትግል በሚፈለገው ደረጃ ውጤት እንዳያመጣ ምክንያት የሆነው ሌብነት /ሙስና ባህል መሆኑና እንደሙብት የተቆጠረበት ደረጃ መድረሱ ነው።

ወቅታዊው አገራዊ የፖለቲካ ችግር እንደሽፋን በመጠቀም ሰዎች ዘርፈው ሲጠየቁ ብሄርንና ሃይማኖትን እንደ ሽፋን በመጠቀም በሙስና ወንጀል ተጠይቀው የፖለቲካ ምህዳርን ለማስፋት በሚል የሚለቀቁ ሰዎች መኖራቸው ሌብነት እንዲበረታታ ስለሚያደርግ ሁሉም በኔነት ስሜት ሊታገለው ይገባል::

በአጠቃላይ ሌብነትና ሌቦች ላይ የተጀመረው አገር አቀፍ ዘመቻ ኮሜቴ ከማቋቋምና መግለጫ ከመስጠት ባለፈ በተጨባጭ ወንጀለኞቹን የማጋለጥና ለህግ አሳልፎ መስጠትን ይጠይቃልና የተጀመረው እርምጃው ተጠናክሮ ይቀጥል እላለሁ::

# ነፃ ሃሳብ



በቀምላቸው አበበ ይማም (ሞሺ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቀምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# በፎርፌ የተረታንበት ቲዊተር ፧

ቲዊተር ኃያልነትንና ሀብትን ያገኘው ከሶስት ማህበረሰቦች ማለትም ከፖለቲከኞች፣ ከታዋቂ ሰዎችና ከጋዜጠኞች ነው ይለናል በዚያ ሰሞን ለንባብ የበቃው የTIME መጽሔት። እነዚህም ተጽዕኖ ፈጣሪ የሕብረተሰብ ክፍሎች ቲዊተርን የመረጡት ሀሳባቸውን ወይም አቋማቸውን በቀጥታ ያለከልካይ ለ238 ሚሊየን መሰሎቻቸው ስለሚያጋሩ ነው። በቀን 500 ሚሊየን ቲዊቶች ዓለምን ያካልላሉ። በተለይ ጋዜጠኞች ተከለ ስዕብናቸውን ለመገንባትና ለዜና የሚሆኑ መነሻ ሀሳቦችን ስለሚያገኙ ቲዊተርን ይመርጡታል። የተቀረው ተጠቃሚ ደግሞ በሌላ መንገድ የማያገኛቸውን ታዋቂ ሰዎችንና ባለስልጣናትን በቀላሉ አግኝቶ ሀሳቡን ለማጋራት ይጠቀምበታል ።

የአሜሪካውን ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን አንቶኒ ብሊንከንን እና ሌሎች ሚኒስትሮችን፤ የሪፐብሊካኖችን ሊቀ መንበር ሮና ማክዳኔልን፤ የዴሞክራቶችን ሊቀ መንበር ጄሚ ሀሪሰን፤ በአጋማሽ ዘመን ምርጫው ዴሞክራቶች ኮንግረሱን ስለተነጠቁ አፈ ጉባኤው የሪፐብሊካኑ ኬቨን ማካርቲ ይሁን አንዲ ቢግስ፤ የቀድሞዋን የዴሞክራቶች አፈ ጉባኤ ናንሲ ፔሎሲን የተካቸውን ሀኪም ጄፍሪስ፤ የኮንግረስና የሴኔት አባላትን፤ ያለምንም ደጅ ጥናት በቀላሉ በቀጥታ የምታገኛቸው በቲዊተር ብቻ ነው።

የአገርን ስም የሚያጠለሹትን እንደ CNN ጋዜጠኛ ኒማ ኤልባገር ያሉ የዋሽንግተን ፖስትና የዘ ኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጠኞችን በቀላሉ በቀጥታ ማግኘት የሚቻለው በቲዊተር ነው። የመንግስታቱ ድርጅት ዋና ጸሐፊን አንቶኒዎ ጉተሬዝንና ተቋማቸውን፤ የአውሮፓ ሕብረት ኮሚሽን ፕሬዚዳንት ኡርሱላ ቮን ዴር ሌዬን፤ የሉላዊነት መገለጫ የሆኑትን እነ የዓለም ባንክ፣ ዓለማቀፍ የገንዘብ ተቋምና የዓለም የንግድ ድርጅት መሪዎችንና ተቋሞቻቸውን፤ መርጦ አልቃሽ የሆኑትን እነ አመንስቲ ኢንተርናሽናልንና ሒውማን ራይትስ ዎችን ከእነ አመራሮቻቸው ያለ ቢሮክራሲና ያለብዙ ውጣውረድ በቀላሉ የሚገኙት በቲዊተር ነው።

በጥቂት ሆሄያት በአንድ ጊዜ ፖለቲከኞችን፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ታዋቂ ሰዎችንና ጋዜጠኞችን መድረስ የሚቻለው በቲዊተር ነው። የዓለም ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳይ የሚመራው በቲዊተር ነው። መደበኛ ሚዲያው ከዚያ ይከተላል ። የአገራት መሪዎችና የዓለማቀፍ ተቋማት ዳናውን ይከተላሉ።

ታዲያ ፖለቲካው፣ ኢኮኖሚውና ሚዲያው እንዲህ በሚዘወርበት የቲዊተር ዓለም ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ መሪዎች፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ ታዋቂ ሰዎችና ጋዜጠኞች የት አሉ ። በጣት ከሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊ ፖለቲከኞች፣ ተጽዕኖ ፈጣሪዎችና ጋዜጠኞች በስተቀር አብዛኛዎቹ የሉም። ያሉትም ቢሆኑ ከተወሰኑት በስተቀር መደበኛ ተሰላፊዎች አይደሉም። በአንጻሩ በፌስ ቡክ፣ በዩቲውብ፣ በቴሌግራም፣ በቲክቶክና በሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች ከሊቅ እስከ ደቂቅ እኔን ጨምሮ ሲራኮት እንታዘባለን።

ይሄን አስመልክቶ የሚወጡ መረጃዎች መሬት ላይ ያለውን ሀቅ ያረጋግጣሉ። ከ64 ሚሊየን በላይ የተንቀሳቃሽ ስልክ ተጠቃሚ ባለበት አገር፤ ወደ 7 ሚሊየን የሚጠጉ የፌስቡክ፣ 6.5 ሚሊየን የሜሴንጀር፣ 826,500 የሊንክዲን፣ 666,900 የኢንስታግራም ተጠቃሚዎች ሲኖሩ የቲዊተር ተጠቃሚዎች ግን ከ35ሺህ አይበልጡም። እነዚህም ገባ ወጣ የሚሉ ናቸው። ንቁ ተሳታፊዎች ደግሞ ከዚህ በእጅጉ ያነሱ እንደሚሆኑ አያጠያይቅም።

የሊንክዲን ተጠቃሚዎች ፊደል የቆጠሩ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ ያላቸው ናቸው ተብሎ ይገመታል። እነዚህ እንኳ የቲዊተር አካውንት ቢከፍቱ ባለ ቲዊተር አካውንቶችን ቁጥር ከ20 እጥፍ በላይ ያሳድገዋል። 120 ሚሊየን ሕዝብ ይዘን፣ እውነትንና ፍትሕን ታቅፈን የአናሳዎች ሀሰተኛ መረጃና ገጽታ ማጠልሸት ሲረታን እንዴት አይቆጨን አያንገበግበንም። በቲዊተር የግጥሚያ ሜዳ ጠላቶቻችን ቀድመው ትጥቃቸውን አሳምረው ቢገኙም እኛ በሰዓቱ ባለመገኘታችን "ዳኛው"በፎርፌ መረታታችንን አርድተውናል።

ሰው ለአገሩ ለአንድያ ህይወቱ ሳይሰስት መስዋዕት እየሆነ እንዴት የቲዊተር አካውንት ከፍተን ለአገር ዘብ መቆም ይሳነናል። የቱንም ያህል ልዩነት ቢኖረን ለአገራችን እውነት መቆም እንዴት ያቅተናል። እነ ማርቲን ፕላውት፣ አሌክስ ድዋልና ጭፍራዎቻቸው የተነሱት፤ ሌት ተቀን ሀሰተኛ መረጃ የሚያንበለብሉት ኢትዮጵያና እና ኢትዮጵያዊነት ቀና እንዳይሉ የመቅበር የምዕራባውያን ታላቅ ሴራ አካል ስለሆኑ እንጂ የዐቢይን አስተዳደር በማዳከም የሚቆሙ ከመሠለን ተሳስተናል። የታሪካዊ ጠላታችን ግብጽ በአገራችን በህቡዕ ያወጀችው የግራጫ ጦርነት አካል መሆኑንም ለአፍታ ልንዘነጋ አይገባም።

የገዥው ፓርቲም ሆነ የተፎካካሪ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች፤ በስፖርቱም ሆነ በኪነ ጥበቡ አንቱታን ያተረፉ ኢትዮጵያውያን፤ የመንግስትና የግል ሚዲያ ጋዜጠኞች፤ ከ100 በላይ በሆኑ የመንግስትና የግል ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስተምሩና የሚመራመሩ በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ምሁራን፤ በዓለማቀፍ ተቋማት የሚሰሩ የበቁና የነቁ ኢትዮጵያውያን፤ በአገር በቀል ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚሰሩ ወገኖቻችን፤ በየሙያ ማህበራቱ ያሉ ዜጎቻችን፤ ወዘተረፈ የት ሄደው ነው እውነትንና ፍትሕን ይዘን በቲዊተር በተደጋጋሚ ፎርፌ እየሰጠን የምንረታው።

በብዙ ነገሮች ላንደሰት፣ በገዢው ፓርቲ ልንከፋ ወይም የፖለቲካ ልዩነት ሊኖረን ይችላል። በአገራችን ግን ልዩነት የለንም። በሀሰተኛ መረጃ ሊያፈርሷት ፣ ገጽታዋን ሲያጠለሿት እያየን እንዳላየን፣ እየሰማን እንዳልሰማን መሆን እንዴት አስቻለን። ደማቸውን አፍስሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው ያቆዩንን አገር፤ ዛሬም እህት ወንድሞቻችን በየጋራ ሸንተረሩ እየተዋደቁላት፤ እንደ ዜጋ ዝቅተኛውን ኃላፊነት መወጣት እንዴት ይሳነናል።

በሞቀ ቤታችን ወይም ቢሯችን ተቀምጠን ስለ አገራችን እውነትና ፍትሕ በቲዊተር እማኝ መሆን እንዴት ይሳነናል። እውነትንና ፍትሕን ታቅፈን እስከ መቼ አስተባባይና ተከላካይ እንሆናለን። አጠቃቀሙን ለመማር ቀላል፣ ብዙ ሰዓት የማይወስድ፣ ኤልሳቤጣዊ እንግሊዘኛ የማይጠይቅ፣ ካልሆነም like እና share ለማድረግ እንዴት እንሰንፋለን። በተለይ ተጽዕኖ ፈጣሪ ታዋቂ ሰዎች እና ባለስልጣናት ባለሙያ ቀጥረው ሀሳባቸውንና አቋማቸውን በንቃት ማጋራት እየቻሉ ለምን በኢቴቪና በፋና እስኪጠየቁ ይጠብቃሉ።

አገራችን ገና ከፊቷ ብዙ ፈተና ይጠብቃታልና ያለ ልዩነት ሰራዊት ልንሆናት ይገባል። በፖለቲካችን፣ በኢኮኖሚያችንና በማህበራዊ ጉዳያችን ብዙኀን ሆነን ሳለ ዝምታን በመምረጣችንና ባለመሳተፋችን አናሳዎች መልካውን ተቆጣጥረው የእነሱ ድምጽ ብቻ ነው ጮሆ እየተሰማ ያለው። ዝምታችንንና ዳር ቆሞ ተመልካችነትንና ኬረዳሽነታችን ሰብረን ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት በመምጣት አገርም ሆነ ትውልድ መታደግ ካልቻልን ነገ እንዳንቆጭ በብርቱ እሰጋለሁ። ትውልድ እንዳይወቅሰን እፈራለሁ።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ካቢኔያቸው በቲዊተር ንቁ ተሳታፊ ቢሆን፤ በተዋረድ ያሉ አመራሮች ይሄን ቢከተሉ፤ የክልሎች ርዕሳነ መስተዳደሮችና የየቢሮ ኃላፊዎቻቸው ይሄን አርዓያ ቢከተሉ፤ የየዩኒቨርሲቲዎች ፕሬዚዳንቶች ግንባር ቀደም ተሳታፊ ቢሆኑ መምህራን ቢከተሉ፤ ከታዋቂና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ጀግናው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ እነ ቀነኒሳን አስከትሎ ቲዊተር ላይ ምሳሌ ቢሆን፤ አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁንና ሌሎች አርቲስቶች ከእነ አድናቂዎቻቸው፤ ገጣሚው፣ ተዋናዩ፣ ጸሐፊ ተውኔቱና አዘጋጁ ጌትነት እንየውና ደቀ መዛሙርቱ፣ አድናቂዎች፣ አርቲስት ሙሉ ዓለምና ተከታይና አድናቂዎቿ፣ ወዘተረፈ በቲዊተር ከአገራቸውና ከሕዝባቸው ጎን ቢቆሙ ሚሊዮኖችን ዳር እስከ ዳር ማነቃነቅ ይቻላል።

በነገራችን ላይ የማህበራዊ ሚዲያን መስፋፋት ተከትሎ ተጽዕኖ ፈጣሪና ታዋቂ ሰዎች ስለ አገርና ስለ ሕዝብ እውነት ድምጽ መሆን በመላው ዓለም እየጎለበተ ያለ ሒደት ነው። መተኪያና ልዋጭ ስለሌላትና ስለ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳር ቆሞ መመልከት ሊበቃ ይገባል። ዝምታን የመረጠው ብዙኀን the silent majority ውድ አገሩን በጫሂ ጥቂቶች the crying minority ዕብሪትና ማንአህሎኝነት አገሩ ስትታመስ እጁን አጣጥፎ በመቀመጥ በታሪክም በትውልድም ተጠያቂ ላለመሆን የዜግነት ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል።

አገራችን ሰላም ልትሆን ነው፤ የተሻለ ቀን ሊመጣነው ብለን ተስፋ ባደረግንበት፤ ብዙኀኖች ዝምታን ስለመረጡ ጥቂት ጽንፈኛ ብሔርተኞች ሰሞኑን ከየጎሬያቸው እየወጡ ሕዝባችንንና አገራችን እረፍት እየነሱት ነው። ብሔርና ሀይማኖት ለይተው አንዱን በሌላው ላይ እየቀሰቀሱ ነው። እንደለመዱት እሳቱ ላይ ቤንዚን እያርከፈከፉ ነው። አበው ሳይቃጠል በቅጠል እንዳሉት መንግስት አደብ ሊያስገዛቸውና ሊያስጠነቅቃቸው ይገባል።

ወደ ተነሳሁበት ነጥብ ስመለስ፤ ባለፉት አራት ዓመታትም ሆነ ዛሬም በተከታታይ ማንነትን ኢላማ አድርገው የተፈጸሙ ጥቃቶች፤ በማንነት ላይ የተዋቀረው አስተዳደር፤ በሀሰተኛ መረጃ የተለወሰው የሴራና የደባ ፖለቲካ፤ መንግስት ጥቃቶችን ሙሉ በሙሉ ቀድሞ መከላከል፣ ተከስተው ሲገኙም ቶሎ ደርሶ ማስቆም አለመቻሉና ሌሎች ደራሽ ምክንያቶች ተደማምረው ልሒቃኑን ሆደ ባሻና አኩራፊ እንዳደረጉት አይካድም።

ሆኖም በእናትና በአገር ስለማይጨከን ቁጥሩ ቀላል ያልሆነ ልሒቅ ኩርፊያም አገር ስትኖር ነውና በሚል በዚህ ክፉ ቀን ከጎኗ በመቆም አለኝታነቱን ያረጋገጠ ሲሆን አብዛኛው ግን ዛሬም በአንድነት መቆም ተስኖታል። ዛሬም ፖለቲካዊ ነጥብ ለማስቆጠር የሚተጋ፤ ቀን እንደጎደለባት አይቶ ይሄን ጊዜ ነው እጇን መጠምዘዝ ብሎ የተነሳ እና አገራዊ ጥሪ ሲቀርብለት እግሩን እየጎተተ ያለው ልሒቅ ብዙ ቢሆንም፤ በአንጻሩ ደግሞ በዲያስፖራም ሆነ በአገር ቤት በዚህ ክፉ ቀን ከአገራቸው ጎን በቆሙና ባልተለዩ ልሒቃን ወገኖች ቲዊተር ላይ ግብግቡ የቀጠለ ቢሆንም በአባዮችና መልቲዎች ብልጫ ተወስዶብናል። በእውነቱ ይህ ያለልዩነት ሊያስቆጨንና በእልህ ሊያነሳሳን ይገባል። ስለቲዊተር ከተነሳ ላይ ዕድልም አደጋም ይዞ ስለመጣው በይነ መረብ ትንሽ ከማለቴ በፊት ስለቲዊተር አጠቃቀም አንዳንድ ነጥቦችን ላነሳሳ ።

ሰዎች በተፈጥሯቸው ሰው ያምናሉ። ስለሆነም የቲዊተር አካውንታችሁን ፕሮፋይል እውነተኛ እንድታደርጉ፤ ማንም ሳይቀድማችሁ ዜናውን ማብሰር፤ በተከታታይ ቲዊት ማድረግ ተመራጭ ቢሆንም በእያንዳንዱ ቲዊት ቢያንስ የግማሽ ሰዓት እንዲኖር፤ ጥያቄ በመጠየቅ ተከታዮቻችሁ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፤ በመደበኛ ህይወትም ሆነ በቲዊተር በተቀረው ማህበራዊ ሚዲያም የመገናኛ ድልድይና አገናኝ ሆኖ መገኘት፤ የቋሚ ተከታዮችን ቲዊት እንደገና ቲዊት በማድረግና በማመስገን ማበረታታት ያስፈልጋል።

ቲዊት የሚያደርገውን መልዕክት በጥንቃቄ መቅረጽ፤ ቲዊት ሲጋራ ወይም ሪቲዊት ሲደረግ የራስ አስተያየት ቢታከልበት ወይም ሪቲዊት ከሚደረገው ሀሳብ ጥቅስ ተመርጦ ከራስጌ ቢሆን፤ ቲዊት ሲደረግ ከ140 ፊደሎች ባይበልጥ ቲዊቱን የሚያጋሩ ሰዎች ሀሳባቸውን ለማከል ዕድል እንዲያገኙ፤ ቲዊትን እንዲያጋሩ ወይም ሪቲዊት እንዲያደርጉ መጠየቅ፤ ምንጭን ማሳወቅ፤ ተከታዮች በተለያዩ አገራት ስለሚገኙ እዚህ ቀን ቢሆን እዚያ ሌሊት ሊሆን ስለሚችልና ቲዊቱ በፍጥነት ሊያልፋቸው ስለሚችል ደግሞ ቲዊት ማድረግ እና ግንኙነትን ማስፋት ሌሎችን መከተል ይመከራል። ስለቲዊተር አንዳንድ ነጥቦችን ካነሳሁ አይቀር እገረ መንገዴን በይነ መረብ ወይም ኢንተርኔት የሚዲያውን መልክዓ እንዴት እንደተጫነውና እንደደረማመሰው ላነሳሳ።

በይነ መረብ የክፍለ ዘመኑን ጋዜጠኝነትም ሆነ የመረጃ ዝውውርን በሁለት መንገድ ተፅዕኖውን አሳርፎበታል። የመጀመሪያው የዜና አጠነቃቀር ባህል እንደገና ከመበየን አልፎ ሒደቱን አመሰቃቅሎታል። በአናቱ የዜጋ ጋዜጠኝነትን citizen journalism ጨምሯል። የእጅ ስልክ፣ ላፕ ቶፕና የዴስክ ቶፕ ባለቤት ሁሉ "ጋዜጠኛ " ሆነ ማለት ነው። ሁለተኛው የበይነመረብ፣ የተግባቦትና የመረጃ ማዕዶች platforms ማለትም ፌስቡክ፣ ዩቲውብ፣ ቲዊተር፣ ቴሌግራምና ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች መረጃን ዴሞክራሲያዊና ተደራሽ በማድረግ የመረጃ የኃይል ሚዛን ከመንግሥትና ከግል የሚዲያ ኩባንያዎች ወደ ሲቪል ማህበራት፣ ጦማሪያን፣ የዜጋ ጋዜጠኞችና ሕዝብ እንዲያዘነብል አድርጎታል።

በይነ መረብ መረጃም ሆነ ሀሳብ የሚዘዋወሩበትን አግባብ ፍጹም ቀይሯል። በቅድመ በይነ መረብ ዘመን መረጃ የሚዘዋወረው የሚተላለፈው በጋዜጣ፣ በመጽሔት፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በፖስታ፣ በመልዕክተኛ፣ በስብሰባ፣ በማህበራዊ አጋጣሚዎች (በቡና፣ በማህበር፣ በእቁብ፣ በዳጉ፣ ወዘተረፈ)ነበር። በድህረ በይነ መረብ ግን መረጃም ሆነ ሀሳብ በፌስ ቡክ፣ በዩቲውብ፣ በቲዊተር፣ በቴሌግራም፣ በኢሜይል፣ ወዘተረፈ በስፋት መዘዋወርና መሰራጨት ጀመረ። በዚህም የመረጃ ተጠቃሚው በይዘትም ሆነ በተደራሽነት የተሻለና ቀላል አማራጭ እንዲኖረው አስችሏል።

ዛሬ ዜናም ሆነ ሌላ መረጃ ለማግኘት የአዲስ ዘመንን እትም፤ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥንን ዜና እወጃና ዝግጅት፤ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎትን መልዕክትና ቴሌግራም አይጠብቅም። በእጅ ስልኩ ሁሉንም ማግኘት ይችላል። ከማህበራዊ ሚዲያዎች ዜናውንም መረጃውንም በቀላሉ መቀራረም ይችላል። ሀሳቡን ለመግለጽም ወደ መደበኛ ሚዲያው መሔድ ሳይጠበቅበት ባለበት ቦታ ባሻው ጊዜ በእጅ ስልኩ አማካኝነት ያጋራል። በይነ መረብ መረጃን ተደራሽና ዴሞክራሲያዊ አድርጓል እየተባለ የሚወደሰውም ለዚህ ነው።

ሆኖም ይህ ተአምረኛ ለውጥ የጥቅሙን ያህል ይዞት የመጣው ጣጣም የትየለሌ ነው። በቅደመ በይነ መረብ ዘመን በመደበኛ ሚዲያው መረጃዎች ከመሰራጨታቸው በፊት በዘጋቢውና በአርታኢው ተጣርተውና ታርመው ያልፉበት የነበረው አሰራር በማህበራዊ ሚዲያው በመቅረቱ ሆን ተብሎ ለሚዛባ መረጃ disinformation፣ ለተሳሳተ መረጃ misinformation እና ለሀሰተኛ ወሬ fake news በር በመከፈቱ የመረጃ መልክዓውን አባጣ ጎርባጣ አድርጎታል።

ለሴራ ኀልዮት conspiracy theory፣ ለውዥንብር የተመቸ በመሆኑ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተቋማትን ክፉኛ እንዲጎዱ፤ የዜጎች ግንኙነት እንዲሻክር፤ ዘረኝነትና ጎሰኝነት እንደ ሰደድ እሳት በቀላሉ እንዲዛመት፤ ጥላቻ ልዩነትና ግጭት እንደ እንጉዳይ እንዲስፋፋ፤ ሕፃናትና ወጣቶች ለወሲብ ፊልም እንዲጋለጡ ከማድረጉ ባሻገር ለወሲባዊ ጥቃት በር ከፍቷል። የማህበራዊ ሚዲያ ሱስ ዜጎችን ለጭንቀትና ለድብርት፤ ቤተሰባዊ ግንኙነትን ለዝንፈት፤ ወዘተረፈ በመዳረግ አገራትን ለተለያዩ ህልቁ መሳፍርት ቀውሶች እየዳረገ እያወዛገበ ይገኛል።

ራሱን " የጋዜጠኝነት ድምጽ "ብሎ እንደሚጠራው እንደ ኮሎምቢያ ጆርናሊዝም ሪቪው CJR መፅሔት የቅርብ ጊዜ ጥናት ከሆነ ከአሜሪካውያን 60 በመቶው ዜና የሚያገኙት ከፌስቡክ ወይም ከቲዊተር ነው። ከ200 ዓመታት በላይ የዳበረ፣ የጎለበተ፣ የደረጀ ዴሞክራሲና ልምድ ያለው መደበኛ ሚዲያ ባለበት አገር ከ10 ሰው ስድስቱ ዜና የሚያገኙት ከማህበራዊ ሚዲያ ከሆነ፤ የዳበረ ነፃና ገለልተኛ የሆነ መደበኛ ሚዲያ በሌላት አገራችንማ ቁጥሩ ወደ 80፣ 90 በመቶ ከፍ ሳይል ይቀራል። ለዚህ ነው ማህበራዊ ሚዲያው ከመደበኛው ባልተናነሰ በሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ ሊጠናከር የሚገባው። ሚዲያዎቻችን ዘመኑን የሚዋጁ መሆን አለባቸው የሚባለው።

ፈጣሪ የአገራችንንና የሕዝባችንን መከራ በቃ ይበለን!!! አሜን።

# ወቅታዊ

# ‹‹ሸሪያችን የፀረ ሙስና ትግሉን ይደግፋል››

- ሼህ አብዱልሐሚድ አህመድ
የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ምክትል ቦርድ ሰብሳቢ

ማህሌት አብዱል


ፎቶ፡- አሸናፊ ጉደታ

**ሙስና ወይም ሌብነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋና የአገር ህልውና ስጋት እየሆነ ከመጣ ውሎ አድሯል። ለሙስናው መስፋፋት የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም በተለይም “ግርግር ለሌባ ይመቻል‹” እንደሚባለው ሁሉ ባለፉት አራት ዓመታት አገሪቱ ለውጥ ላይ መሆኗ እንዲሁም ለሁለት ዓመታት በሰሜኑ አካባቢ ሲካሄድ የነበረውን ግጭት ለሌቦቹ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ ይነሳል። መንግስት ከሰላም ስምምነቱ ማግስት ጀምሮ የአገር ህልውና ስጋት የሆነውን ሙስና ለመዋጋት ቆርጦ መነሳቱን አሳውቋል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ በፌደራል ደረጃ የፀረ- ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ አቋቁሟል። ይህንን ተከትሎም የአዲስ አበባ አስተዳደሩም በተመሳሳይ መንገድ ኮሚቴ አቋቁሞ ትግሉን ጀምሯል።**

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ብሔራዊ ኮሚቴው መቋቋሙን በገለጹበት ወቅትም ሙስና አገርን የሚበላ ነቀዝ ስለመሆኑና የአገርን አንጡራ ሀብት እየቦረቦረ ጥሪቷን ባዶ ስማስቀረት ሌት ተቀን የሚማስን ተባይ እየሆነ መምጣቱን ተናግረዋል። ዋልጌ ባለሥልጣናት፣ በፍቅረ ነዋይ የታወሩ ደላሎች እና ባለሃብቶች አንድ ላይ ሲገጥሙ፤ ከነዚህ የሌብነት ፊታውራሪዎች ጀርባ ብዛት ያላቸው ዜጎች መሰለፍ ሲጀምሩ ሙስና የተባለው ነቀዝ አገርን እንደ ወረርሽኝ የሚያጠቃት መሆኑንም አንስተዋል። በተለይም የአገርን ልማት አጥንቱ ድረስ እስከ መጋጥ ከደረሰ ሙስና አንድ አደገኛ ወረርሽኝ መሆኑን ነው የተናገሩት። ጠቅላይ ሚኒስትሩ €€ሙስና ዛሬ የአገራችን የደኅንነት ሥጋት ሆኗል። ወደ ብልጽግና የምናደርገውን ጉዞ እጅ ተወርች አሥሮ ለመያዝ ከጠላቶቻችን እኩል ሙሰኛው እየታገለን ነው። የተስተካከለ ቢሮክራሲ፣ የተቀናጀ መዋቅርና ዘመናዊ አሠራር ለሙስና ተጋላጭነትን ስለሚቀንሱ፣ እነዚህን ለማጥፋት ወይም ለማሰናከል ሙሰኛው ቀን ከሌት እየሠራ ነው‹‹ በማለት ጠቅሰዋል።**

**መንግሥት በየደረጃው የሚገኘውን መዋቅር በመፈተሽ፣ አዳዲስ አሠራሮችን በመዘርጋት፣ በቴክኖሎጂ የታገዙ ሥራዎችን እያሳለጠ ሥራዎችን ከእጅ ንክኪ ነጻ በማድረግ፣ በሙስና ወንጀል የሚሳተፉ አመራሮችንና ሌሎች ተዋንያንን ለሕግ በማቅረብ፣ ሙስና ምቹ ሁኔታ እንዳይፈጠርለት ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን አስታውሰዋል። ነገር ግን አገሪቱ ያጋጠማትን ጦርነትና ኮሮናን የመሳሰሉ ወረርሽኞች የመንግሥትን ትኩረት ወስደዋል ብለው ያሰቡ ሙሰኞች፣ በየቦታው ተሠግሥገውና ኔት ወርክ ዘርግተው፣ ኢትዮጵያን ለማጥፋት እየሠሩ መሆናቸውን ነው ያመለከቱት። ይሄን የአገር ትልቅ ስጋት የሆነውን ሙስናን በመዋጋት ረገድ የሀይማኖት አባቶች ሚና ምን መሆን አለበት በሚሉና በተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከኢትዮጵያ እስልምና ጠቅላይ ምክር ቤት ሥራ አስፈፃሚ አባልና ከኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ምክትል ቦርድ ሰብሳቢ ከሆኑት ሼህ አብዱልሐሚድ አሕመድ ጋር ቃለምልልስ አድርጓል። ይህም እንደሚከተለው ስንባብ ቀርቧል።**

**አዲስ ዘመን፡- ሙስናን በሚመለከት እስልምና አስተምህሮ ምን እንደሚመስል ያብራሩልንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**ሼህ አብዱልሐሚድ፡-** በመጀመሪያ አገራችን ኢትዮጵያ ከጦርነት አውድማ ወጥታ በአሁኑ ወቅት ደግሞ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጀምሮ እስከ ታች ድረስ የፀረ-ሙስና ትግል የተጀመረበት ጊዜ በመሆኑ ያለኝ ደስታ መግለፅ እወዳለሁ። በሁለተኛ ደረጃ ሙስናን በማጥፋት ረገድ ህብረተሰቡን የማንቃትና የማሳተፍ ትልቅ ስራ ነው፤ ይሄ ሊበረታታ እንደሚገባ መናገር እወዳለሁ። ከዚህ አንፃር አሁን ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ሙስና የአገር ደህንነት ስጋት ሆኖ እየመጣ በመሆኑ መንግስት ለሙሰኞች ምቹ ሁኔታ እንዳይፈጠር ለማድረግ መስመር ዘርግቷል። እኛም የኃይማኖት አባቶች ወይም የእምነት ተከታዮች ህብረተሰቡን ያማረሩ ቡድኖች እና ግለሰቦችን የማጋለጥ ስራ እንድንሰራ ሰፊ ትምህርት እየተሰጠ ነው የሚገኘው።

ወደ ጥያቄው ስመለስ ሙስና ከቁርዓንም፤ ከሃዲስም አንፃር በብዙ መንገድ የተወገዘ ተግባር መሆኑ መላው ሙስሊም የሚያውቀው ነው። ሙስና ውስጥ የሚዘፈቅ፣ ገንዘብ ያለአግባብ ከህብረተሰቡ የሚሰበስብና ሃብት የሚያካብት ሰው አንደኛ አገር መምራት እንደማይችል በቁርዓን ላይ በግልፅ ተቀምጧል። ነብይ ሱሌይማን (ንጉስ ሰለሞን) ንግስት ሳባን ወደ ራሱ እምነት ለማምጣት ጥሪ ባደረገላት ጊዜ እሷም ይሔ ሰው ትክክለኛ ነብይ መሆኑን የምትለይበት ዘዴ አሰበች እና አንድ ሺ አሽከሮችን እንዲሁም አጥር ግንብ ለመገንባት እና ቤት ለመስራት የሚያስችሉ ወርቆችን አዘጋጀች። በተጨማሪም የነገስታት አልባሳትን አቀረበች እና እነዚህን ቁሳቁሶች በመያዝ በሄደችበት ጊዜ ንጉስ ሰለሞን ተቆጣ። ‹‹ለእኔ ፈጣሪ የሰጠኝ የነብይነት እና የንግስና ማዕረግ ይበልጥብኛል ›› በማለት ንግስቲቱ ያቀረበችለትን ስጦታ አለመቀበሉን ቅዱስ ቁርዓን ይናገራል። በዚህም ንግስቲቷ ጉቦ የማይቀበል ትክክለኛ ንጉስ መሆኑን አጣራች ማለት ነው። በአጠቃላይ ሙሰኛ የሆነ ሰው አገር መምራት እንደማይችል ይህ የቅዱስ ቁርዓን ክፍል ያስረዳል።

ሌላው ስለሙስና የተወገዘ ተግባር ስለመሆኑ የሚያስተምረን የቁርዓን ክፍል ደግሞ በእኛው አገር የተፈጠረ ነው። ይኸውም የንጉስ ነጃሺ ታሪክ ነው። እንደሚታወቀው እኚህ ንጉስ በእስልምና ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያላቸው ሲሆን እስልምናን የተቀበሉና ነብዩ መሃመድ የላኳቸውን ሰዎች በአክብሮት ተቀብለው ያኖሩ ሰው ናቸው። በታሪክ እንደሚታወቀው እነዚህን የእስልምና ተከታዮችን በራሳቸው ወገኖች ከገዛ አገራቸው ተሳድደው ወደ ኢትዮጵያ በመጠቡት ጊዜ እነዚያ አሳዳጆች ለንጉስ ነጃሺ ስጦታዎችንና የተለያዩ መደለያዎችን በመያዝ የነብዩ መሃመድን ባልደረቦች አሳልፈው እንዲሰጧቸው ይጠይቋቸዋል። እነዚህ ሰዎች የነብዩን ባልደረቦች እግራቸውን ቀፍድደው በሰንሰለት አስረው ወደ አገር ለመመለስ ፍላጎት የነበራቸው ቢሆንም ንጉሱ ግን በቀረበላቸው ስጦታዎች እና መደለያዎች ሳይታለሉ አምነው የተጠጓቸውን ሰዎች ህይወት ታድገዋል። ሚዛናዊ እና ፍትሓዊ መሪ ስለነበሩም እነዚህን ሰዎች ተራራ በሚያክል ወርቅ አለውጣቸውም በሚል አሳልፎ ያልሰጡ ትልቅ መሪ ናቸው። ከዚህም ታሪክ ጉቦን ባለመቀበልና የሚሰጡትን በማውገዝ ፍትሃዊ መሪ መሆን እንደሚያስፈልግ ከንጉስ ነጃሺ እንማራለን።

እንዲሁም ነብዩ መሃመድ ያለአግባብ የሚያካብቱት ሃብት ለጀሃነም እሳት ቅርብ እንደሆነ ተናግረዋል። አላህም በቁርዓን ላይ የሰውን ሃብት የምታስተዳድሩ፤ ሃብታም የድሃውን፤ ተበዳሪ አበዳሪውን፤ በጥቅማጥቅም ተደልላችሁ የሰውን ገንዘብ ያላግባብ አትንኩ በማለት ይናገራል። የህብረተሰብንም ገንዘብ ያለአግባብ የሚያግበሰብሱ ሰዎች የቂያማ ቀን (በፍርድ ቀን) ጀሃነም (ገሃነም) እንደሚወርዱ በቁርዓን ላይ በግልፅ ተቀምጧል። በተጨማሪም እያንዳንዱ ሙስሊም ነገ የቂያማ ቀን የገንዘቡን ምንጭ ይጠየቃል። እንደዚሁም ‹‹ሙሰኛ የሆነ፤ ጉቦ የሚበላ፤ ያለአግባብ ሃብት የሚያፈራ ሰው የሚያደርገው ፀሎት ተቀባይነት የለውም›› ይላል። ነብዩ መሃመድም አንድ ጊዜ ከሃብታሞች ለድሃ ዘካ የሚሰበስቡ ሰዎች መደቡና ያለአግባብ እንዳይሰበስቡ ማስጠንቀቂያ ሰጧቸዋል። ‹‹እኛ ሹመት ሰጥተነው መርፌ እንኳን የደበቀ ሰው ነገ የቂያማ ቀን ተዋርዶ ተሸክሞ ይዟት ይመጣል›› በሚል በግልፅ ተናግረዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ከሀይማኖቱ አስተምህሮ አንፃር ታዲያ ሙስንና የመከላከሉ ኃላፊነት የማን ነው ብለው ያምናሉ?**

**ሼህ አብዱልሐሚድ፡-** በእኔ እምነት ኃላፊነቱ የሁላችንም ነው፤ ምክንያቱም ማናችንም ከተጠያቂነት ስለማናመልጥ። ከዚህ አኳያ ቤተ-እምነት ውስጥ ስለሙስና ብዙ መናገር ይቻላል። ይሁንና ቅድሚያ ከራሳችን፤ ከቤተ-እምነታችን ውስጣዊ አሰራር መጀመር አለብን። በሌሎች ላይ ጣት ከመቀሰራችን በፊት ከሙስና ነጻ ነን ወይ ብለን ራሳችንን መፈተሽ አለብን። በየጊዜው እኛም ላይ የሚነሱ ብዙ ሃሜቶች አሉ። ቤተ-እምነቶች ራሳችን ሙስና ውስጥ ተዘፍቀን እንዳለን በብዙ መንገድ ሲነገር እናደምጣለን። ስለዚህ በስልጣን እና በገንዘብ ላይ ከራሳችን ጀምረን ውሳኔ መወሰን አለብን። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይም እንዳሉት በመንግስትም ሆነ በእምነት ተቋማት ያለን መሪዎች ለህዝቡ መስራት ካልቻልን ከእናቶቻችን መቀነት ላይ ፈትተን ሰርቀን አንበላም። እኛ ደግሞ ቤተ-እምነቶች ከዚያ በላይ ይህ ጉዳይ ሊያሳስበን ይገባል። ህብረተሰቡ እኛን አምኖ የሚሰጠንን ሃብት በሚገባው ቦታ ላይ አውለን ድህነትን የመቀነስ ስራ መስራት አለብን የሚል እምነት አለኝ።

በመሰረቱ ሙስና ላይ የሚሳተፉ ሶስት አይነት ሰዎች ናቸው። አንደኛው ሰጪ ነው፤ ሁለተኛው ተቀባይ ነው፤ ሶስተኛው በመሃል የድለላ ስራ የሚሰራው አካል ነው። እነዚህን ሰዎች ነብዩ መሃመድ ረግመዋቸዋል። ጉቦ ሰጪውም ሆነ ተቀባዩም እንዲሁም ደላላው የተረገመ ሰው መሆኑን በግልፅ ነው በቅዱስ ቁርዓን የተቀመጠው። ትልቁ ሊሰመርበት የሚገባው ሙስና ከሰው ህይወት የተሳሰረ መሆኑን ነው። ከህፃናት እና ከእናቶች ህይወት ጋር የተሳሰረ ነው። ለምሳሌ አንድ ጉምሩክ ላይ የሚሰራ ሰው ጊዜው ያለፈበት ወተት ወይም መድሃኒት ጉቦ ተቀብሎ እንዲገባ ቢያደርግ በፈጣሪ ዘንድ የሰው ህይወት በማጥፋት ተጠያቂ ነው የሚሆነው። ነገ የቂያማ ቀን የሰው ልጆችን ሁሉ እንዳጠፋ ተደርጎ ነው አላህ የሚጠይቀው። ስለዚህ የሃይማኖት አባቶችም፤ መንግስትም ቢሆን ከጠያቂነት አያመልጡም። ሆኖም አሁንም ድረስ የተወሰኑ ሰዎችን ኪስ ለማደለብ ተብሎ ለሰው ጤና አደጋ የሆኑ በተለይ ካንሰር ሊያመጡ የሚችሉ ምርቶች በሙስና ሲገቡ ይስተዋላል። እንዲህ አይነቱን ለህዝብም ሆነ ለአገር ደህንነት ስጋት የሆነ ችግር ለማስቀረት የእምነት አባቶች ትልቅ ሚና አለን ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ሙስናን ወይም ሌብነት የሚያወግዙ የቀደሙ እሴቶቻችን እየተሸረሸሩ መምጣታቸው ይነገራል። በእርሶ እምነት ምክንያቱ ምንድን ነው? እነዚህን እሴቶች በመመለስ ረገድ የሃይማኖት ተቋማት ድርሻ ምን ሲሆን ይገባል?**

**ሼህ አብዱልሐሚድ፡-** በመጀመሪያ ደረጃ ሁላችንም ከህዝብ አብራክ የወጣን የህዝብ አገልጋዮች እንደመሆናችንና በእነዚህ መልካም እሴቶች ተቀርፀን ያደግን በመሆኑ አሁን ላይ የእሴቶችን መሸርሸር ያሳስበኛል። አሁን ላለንበት ጥሩ ማንነት ቤተሰቦቻችን በዚህ እሴት ለፍተው ማሳደጋቸው እንደሆነ የሚካድ አይደለም። ለእሴቶቻችን መሸርሸር በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም በእኔ እምነት ግን ለግላቸው ጥቅም ብቻ የሚያስቡ ሰዎች እየተበራከቱ በመምጣታቸው ነው። ይህንን እሴት በመመለስ ረገድ በተለይ የእምነት አባቶች ለስራችን ልዩ ትኩረት እና ክብር ሰጥተን ህብረተሰቡን ልናገለግል ይገባል። ሙሰኝነት ህብረተሰቡን ሊጎዳና እሴት ሊሸረሽር የሚችል፤ ወደ ድህነት የሚመራ አፍሪካንም ጨምሮ ችግር ነው።

እንደሚታወቀው በአንድ አገር መተሳሰብና በሃቅ የሚሰራ ሲጠፋ እንዲሁም ፍትህ ሲጓደል ዜጎች ሳይወዱ በግዳቸው ለስደት ይዳረጋሉ። በሙስና ምክንያት ለአገር ልማት ሊውል የሚገባው ሃብት በጥቂት ሰዎች እጅ ውስጥ በመግባቱ ህዝቡ በድህነት ውስጥ ይማቅቃል። እነዚህን አካላት የሚያወግዙ የቀደሙት እሴቶቻችን እየተረሱ በመምጣታቸው ችግሩ እየተባባሰ መጥቷል። እዚህ ላይ ሁላችንም ከዚህ ህብረተሰብ እንደመውጣታችን ለዚህ ህዝብ አገልጋይ ሆነን የምንሰራ ከሆነ ሃገሪቷን ከችግር ማውጣት እንችላለን ብዬ አምናለሁ። በመሆኑ የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት ከግጭት ከመለያየት ወጥተን እጅ ለእጅ ተያይዘን ልንሰራ ይገባል።

በተለይም እያንዳንዱ ቤተ እምነት ምዕመኑን በሚገባ ሊያስተምርና በጥሩ ስነ-ምግባር የታነፁ እንዲሆኑ መሥራት ይጠበቅበታል። እርግጥ ነው፤ ካሜራ አስቀምጠን ሰዎችን መቆጣጠር ይቻል ይሆናል፤ ከዚህ በላይ ግን ጠቃሚው

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ



**ቤተ-እምነት ውስጥ በእግር ብቻ ሄዶ አገልግሎት የማይገኝበት ሁኔታ አለ፤ የሆነ ነገር ካልሰጠን በችሎታ ብቻ ሃላፊነት አይሰጥም፡፡ በመሰረቱ ገንዘብ ብቻ መቀበልና መስጠት አይደለም ችግሩ፤ ያለ ችሎታ በዝምድና ብቻ መቅጠርም ሙስና ነው**

ነገር ሰዎች አላህን የመፍራት ስነልቦና ነው ሊኖራቸው የሚገባው። ምክንያቱም በእምነቱ የፀና እና ፈጣሪውን የሚፈራ ሰው ህዝብን ሊበድል አይችልም። ለዚህ ሁላችንም፤ ከአገራችን ከመንግስታችን ጋር መቆም መቻል አለብን። ሁላችንም ውስጣችን ከፈተሽን፤ ከህብረተሰቡ እሴት አፈንግጠው የሚወጡትን ከገሰፅንና እጅ ለእጅ ተያይዘን ከሰራን ሙስናን ዘረኝነትን ጦርነትን ግጭትን ማስቀረት እንችላለን።

እርግጥ እሴቶቻችንን ከመመለስ አኳያ እንደእምነት ተቋም ብዙ የሚጠበቁብን ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ እኛ ራሳችን ለምዕመኑ አርዓያና ምሳሌ መሆን መቻል አለብን። ሁለተኛ መግባባት፤ በፍቅር ማስተማር ይጠበቅብናል። አንድ ግለሰብ ሙስና የማይቀበል፤ ከሙስና ንፁህ የሆነ፤ የሰውን ገንዘብ ያለአግባብ የማይቀበል፤ ደሞዙን በአግባቡ የሚጠቀም ከሆነ በተቋሙ ውስጥ ፍቅርንና እውነተኝነትን ነው የሚያስተምረው። ሌሎቹም የእሱን አርዓያ እንዲከተሉ ያደርጋል። በሰላም ወጥቶ በሰላም ሳይፈራ ይገባል። ከሙስና ንፁህ የሆነ ሰው ቤቱን በኤሌትሪክ ሽቦ ማጠር አይፈልግም። መሳሪያ አይታጠቅም፤ ጋርድም አይፈልግም። ስለዚህ ንፁህ ሆነን ከህብረተሰቡ ጋር መኖር የምንፈልግ ከሆነ ለዘላለም የተሸለሙና ጥሩ ስም ይዘው የሚያልፉ ናቸው።

በተቃራኒው ያለአግባብ ገንዘብ የሚሰበስቡና ጉቦ የሚቀበሉ ሰዎች በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያጠራቀሙትን ገንዘብ ሳይበሉት ነው የሚያልፉት። ይህ ደግሞ ከራሳቸው አልፎ ልጆቻቸውም ሳይቀሩ በእነሱ መንገድ የሚመሩ ከመሆናቸውም ባሻገር በራሳቸው የማይታመኑ ነው የሚያደርጓቸው። ስለዚህ ሁላችንም ኢትዮጵያን ለማስቀጠል፤ ከድህነት ለማውጣት በየቤተ-እምነታችን ያለው ብልሹ አሰራር ልንፈትሽ ነው የሚገባው። ከአያት ከቅድሚያት የወረስነው እሴቶቻችን በማስቀጠል ይህችን አገር ትልቅ ደረጃ ላይ ማድረስ ነው ያለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሃብት እያፈሩ ያሉትን የእምነት ሰዎች በመመለስና ምዕመናኑን በማስተማር ረገድ ምን ያህል ሚናችንን ተወጥተናል ብላችሁ ታስባላችሁ?**

**ሼህ አብዱልሐሚድ፡-** እንደእኔ እምነት በሙስና ላይ የሚገባንን ያህል ሰርተናል ብዬ አላምንም። አሁንም ድረስ ሙስና በመንግስት አካላት ብቻ የሚፈፀም አድርጎ የሚቆጥረው በርካታ ነው። ትላልቅ ባለስልጣናት ንብረታቸውን እንዲያስመዘግቡ መደረጉም ሆነ በመንግስት በሙሰኞች ላይ የጀመረውን እርምጃ መበረታታት እንዳለበት አምናለሁ። በመሰረቱ ሸሪያችን የጸረ ሙስና ትግሉን ይደግፋል። ሆኖም የሙሰኝነትን ፀያፍነት አርአያ ሆነን በመገኘትም ሆነ ጠንከር ያለ ትምህርት በመስጠት አልሰራንም። ይህንን ጉዳይ ወደ እኛ ተቋም ካመጣሽው ከዚህ ቀደም ሙስና ሲበላ የነበረ ሰው ታውቆበት ቢነሳም አፉ (ይቅርታ) በመባባል እንዲታለፍ በማድረግ ተቋሙ እየወደመ የሄደበት ሁኔታ አለ። ከዚህ አንፃር ሙስና ብዙም ትኩረት ሰጥተን አስተምረናል ወይም ኃላፊነታችንን ተወጥተናል ብዬ አላምንም።

**አዲስ ዘመን፡- ከሴብነት የፀዳ አሰራር በመዘርጋት ረገድ የተቋማቱ ተሞክሮ ምን ይመስላል?**

**ሼህ አብዱልሐሚድ፡-** ቤተ-እምነቶች ከሙስና የፀዱ ናቸው ብዬ አላምንም። ምክንያቱም ደግሞ ብዙ የሚታዩ ችግሮች በመኖራቸው ነው። አንድ ሰው ባለው መንፈሳዊ እውቀት፤ ችሎታ፤ በስራ ልምድና የትምህርት ደረጃ ታይቶ አይቀጠርም። በዝምድና ነው ቤተ-እምነት ላይ የሚቀጠረው። ይሄ ግልፅ ነው። አብዛኛው ቤተ-እምነት በዝምድና የተሞላበት ነው፤ እኔም ከሹፌር ጀምሮ ዘመዴን ስቀጥር፤ ሌላውም እንዲሁ በማድረግ የዘመድ ተቋም ነው የሆነው። በነገራችን ላይ በሙስና አገር እያጠፋ ያለው ቤተ-እምነት ውስጥ ያለው አሰራር ጭምር ነው። አስቀድሜ እንደገለፅኩልሽ ሌላውን ከመኮነን እና ተጠያቂ ከማድረግ አኳያ እኛም ውስጥ ያለው ችግር ሊፈተሽ ይገባል።

ቤተ-እምነት ውስጥ በእግር ብቻ ሄዶ አገልግሎት የማይገኝበት ሁኔታ አለ፤ የሆነ ነገር ካልሰጠን በችሎታ ብቻ ኃላፊነት አይሰጥም። በመሰረቱ ገንዘብ ብቻ መቀበልና መስጠት አይደለም ችግሩ፤ ያለ ችሎታ በዝምድና ብቻ መቅጠርም ሙስና ነው። በእምነታችንም ነብያችን ቂያማ መቼ ነው ብለው ሲጠይቋቸው « እውቀቱና ችሎታው የሌለው ሰው ያለቦታው ያስቀመጡት ቀን ነው» ብለው የመለሱት። ይህ ሲሆን ተቋም ብቻ ሳይሆን አገር ይተርፋል። አሁን ላይ እኮ በየፍርድ ቤቱ ጉዳዮቻቸው በጊዜ ማለቅና ውሳኔ ማግኘት ሲገባቸው ገንዘብ ካልሰጡ ያለአግባብ የሚንከራተቱበት፤ ዳኛ ገንዘብ ወስዶ ፍትህ የሚያዛበበት፤ ምስክሮች በሃሰት ምስክር ሆነው ንፁሃን የሚበደሉበት አጋጣሚ በርካታ ነው። ይህ ሁሉ የሆነው ሙስና ስለተስፋፋ መሆኑ ግልፅ ነው። ችግሩ ደግሞ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ብቻ ሳይሆን በቤተእምነት ውስጥም ተንሰራፍቷል። በሚገርም ሁኔታ ስፖርት ውስጥ እንኳን በስፋት ይታያል፤ ጉቦ ያልሰጠች ሯጭ ችሎታ እያላት ሌላው በዝምድና እና በጉቦ እንዲያልፍና እሷ እንድትወድቅ ይደረግና ዜግነቷን ቀይራ ለሌላ አገር ለመሮጥ ትገደዳለች። በእምነት ቤቶች ውስጥም ያለው ችግር ተመሳሳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ እድሉን ልስጥዎት?**

**ሼህ አብዱልሐሚድ፡-** ለእምነት ተከታዮቹ እንዲሁም ለሁሉም ቤተ- እምነት ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት አስቀድሜ እንዳነሳሁት ህዝብ መምራትና አገር ማስቀጠል የሚቻለው ከሙስና ስንፀዳ ብቻ መሆኑን ተገንዝበው ለዚህም ሁላችንም ቁርጠኛ መሆን እንዳለብን ነው። ንጉስ ነጃሺ ፍትሃዊ መሪ መሆን የቻሉት ሙስናን በመታገሉ ነው። የቱንም ያህል መንፈሳዊ ነን ብንል ሙሰኞች ከሆንና ሙሰኞቹንም በግልፅ የማንታገል ከሆነ ከአላህ ፍርድ የማናመልጥ መሆኑን መገንዘብ ይገባናል። ሙስና ለእምነት ተቋሞቻችንም ሆነ ለአገራችን ህልውና አደጋ መሆኑን ተገንዝበን እያንዳንዳችን መታገል አለብን። ሙስናን ተሸክመን ፀሎታችን ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም፤ ንፁህ አዕምሮና እንቅልፍም አይኖረንም።

በመሰረቱ አገር ተረካቢ ትውልድ እንዲኖር የሚሻ ሰው ራሱን ከሙስና መቆጠብ ይገባዋል። እንደዚህ መንግስት የጀመረውንና ሚዲያዎች ይህንኑ ሙስና ለመታገል እያደረጋችሁት እንዳላችሁት ጥረት እኛም ቤተ-እምነቶች ሙስናን በይፋ ልናወግዝ ይገባል። ይህንን ማድረግ ካልቻልን ችግሩ መልሶ እኛኑ መጉዳቱ አይቀርም። ምክንያቱም ሙስና በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ የኑሮ ውድነቱ ይባባሳል፤ ይህም ደግሞ በዜጎች ላይ ትልቅ ጫና ይፈጥራል። በየመጋዘኑ ምርት በማከማቸት የድሃውን ችግር የሚያባብሱ ነጋዴዎችም ከዚህ ተግባራቸው እንዲታቀቡና ከፈጣሪ ፍርድ እንዲያመልጡ ለማሳሰብ እወዳለሁ።

እዚህ ጉዳይ ላይ እኛም ቤተ-እምነቶች ከፍተኛ ስራ መስራት መቻል አለብን። በተለይ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና የማስተማሩን ስራ በስፋት ልናካሂድ ይገባል። ይህንንም ሸሪአው ስለሚፈቅድልን አገሪቷን መጠበቅ የሚፈልግ ሰው ወደ ማጋለጥ ስራ መሄድ ነው ያለበት። በነገራችን ላይ ሙስናን የመታገሉ ጉዳይ ለነገ የሚተው ስራ ሳይሆን በአፋጣኝ ልንከውነው የሚገባ ተግባር ነው። ይህንን በምናደርግበት ሰዓት ሙሰኞቹ ተጨማሪ ችግር በአገር ላይ ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ግልፅ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ መንግስት ጥንቃቄ ሊያደርግበት ይገባል ባይ ነኝ።

ለምሳሌ አስር ሰው ቢታሰር ሌሎቹ ያከማቸውን ንብረትና ዶላር እናጣለን በሚል በአገር ላይ ሌላ ችግር ሊፈጥሩና ወደ ውጭ ሊሸሹ ይችላሉ። ለዚህ ደግሞ ሰንሰለት ፈጥረው የአገሪቱን ኢኮኖሚ የሚቆጣጠሩበት ሁኔታ አለ። ስለዚህ ይህንን መንግስትም ሆነ እኛ የእምነት ሰዎች አስቀድመን ተገንዝበን ዋጋ የሚያስከፍልም ቢሆን በግልፅ መታገልና ማጋለጥ ይገባናል። በአጠቃላይ ሁላችንም አገራዊና ህዝባዊ ኃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል። በተለይ ቤተ-እምነቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር በጁምዓውና በየእሁድ ስብከት ምዕመናኖቻችንን ማስተማር ይጠበቅብናል። በተለይ እኛ የእስልምና እምነት ተከታዮች አገሪቱ ከሙስናና ከሙሰኞች የፀዳች እንድትሆን ለማገዝ ዝግጁ መሆናችን ለማሳወቅ እፈልጋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ሼህ አብዱልሃሚድ፡-** እኔም በዚህ ጉዳይ ላይ ሃሳብ እንድሰጥ እድሉን ስለሰጣችሁኝ ላመሰግን እወዳለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## አገር በቀል አምራቾችን ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የመሳብ ጥረት

አንተነህ ቸሬ

ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር እያከናወነች ባለችው ተግባር ለኢንዱስትሪ ልማት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ትገኛለች። በግሉ ዘርፍ በኢንዱስትሪው መስክ እየተከናወኑ ካሉ ተግባሮች ጎን ለጎን መንግስት እስከ አሁን 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ገንብቶ ወደ ስራ አስገብቷል። በኢንዱስትሪ ፓርኮቹም ተዋቂ ዓለም አቀፍ የውጭ ባለሀብቶች ገብተው ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እያቀረቡ ናቸው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ፓርኮቹ እየገቡ ይገኛሉ።

በአገሪቱ የሚገኙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በበላይነት የሚያስተዳድረው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ባለፈው ሳምንትም ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ለማምረት ፍላጎት ካላቸው ሦስት ኩባንያዎች ጋር ስምምነቶችን ተፈራርሟል። ከኮርፖሬሽኑ ጋር ስምምነት የተፈራረሙት አምራቾች ‹‹ሎንግ ማርች ኤሌክትሪካል ኢኪዩፕመንት ማኑፋክቸሪንግ›› ኩባንያ (Long March Electrical Equipment Manufacturing PLC)፣ ‹‹ዋርቃ ትሬዲንግ›› ኩባንያ እና ‹‹ኤን ኬ ወርልድ ሜዲካል ኢኪዩፕመንት ማኑፋክቸሪንግ›› (NK World Equipment Manufacturing PLC) ሲሆኑ ሁለቱ አገር በቀል አምራቾች፣ አንዱ ደግሞ የውጭ ድርጅት ነው። አምራቾቹ ከ480 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል ይዘው ወደ ሥራ ይገባሉ፤ ከ550 በላይ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያንም የሥራ እድል ይፈጥራሉ ተብሎም ይጠበቃል።

‹‹ሎንግ ማርች ኤሌክትሪካል ኢኪዩፕመንት ማኑፋክቸሪንግ›› ኩባንያ (Long March Electrical Equipment Manufacturing PLC) የውጭ ኩባንያ ሲሆን፣ በ240 ሚሊዮን ብር ካፒታል የኤሌክትሪክ ቆጣሪዎችንና ሌሎች የኤሌክትሪክ መሳሪያዎችን በማምረት ተግባር ላይ ይሰማራል። ኩባንያው የምርት ሥራውን በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ በሦስት ሺ ካሬ ሜትር የማምረቻ ሼድ ላይ የሚያከናውን ይሆናል። ምርቶቹን ለአገር ውስጥና ለውጭ አገራት ገበያዎች የማቅረብ እቅድ ያለው ይህ ድርጅት፣ ለ250 ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥርም ይጠበቃል። ኩባንያው በብዛት ከሰው ኃይል ይልቅ በቴክኖሎጂ የታገዘ አሰራርን የሚጠቀም እንደሆነም ተገልጿል።

አገር በቀሉ ‹‹ዋርቃ ትሬዲንግ›› ኩባንያ ክር በማምረት ሥራ ላይ የሚሰማራ ሲሆን፤ በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ 5500 ካሬ ሜትር መሬት በመከራየት ወደ ምርት ሥራ ይገባል። ኩባንያው የተለያዩ የክር ዓይነቶችን ያመርታል። ከሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ በተጨማሪ በሌሎች ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ አምራቾችም የክር ምርቶችን የማቅረብ እቅድ አለው። ይህም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የግብዓት ትስስር በመፍጠርና በምርት ሂደት ላይ የሚፈጠር የግብዓት እጥረትን በመፍታት የምርት አቅርቦትንና የወጪ ንግድ ገቢን ለማሳደግ ይረዳል።

የ‹‹ዋርቃ ትሬዲንግ›› ኩባንያ ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዮሴፍ ምስጋናው ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብቶ ማምረት ብዙ ቢሮክራሲያዊ ውጣ ወረዶችን እንደሚያቃልል ይገልጻሉ። ‹‹መሬት ወስዶ ለማልማት ቢሮክራሲው ረጅም ጊዜ ይወስዳል። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግን ሁሉንም አገልግሎት መስጠት ስለሚችሉ ወደ ፓርኮቹ ገብቶ መሥራት ተመራጭ ነው›› ይላሉ። ከተመሰረተ ሁለት ዓመታትን ያስቆጠረው ‹‹ዋርቃ ትሬዲንግ›› ክር በማምረት ላይ እንደሚሰማራ ጠቁመው፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ኩባንያዎችም ምርቶቹን እንደሚጠቀሙ ይናገራሉ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ የአገሪቱን የክር ምርት ግብዓቶች ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ ለማምረት ኩባንያቸው በቤንሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች ጥጥ በማልማት ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

‹‹ኤን ኬ ወርልድ ሜዲካል ኢኪዩፕመንት ማኑፋክቸሪንግ›› (NK World Equipment Manufacturing PLC) ከኮርፖሬሽኑ ጋር ስምምነት የተፈራረመው ሌላኛው አገር በቀል ኩባንያ ነው። ኩባንያው በቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ አንድ ሄክታር የለማ መሬት ተረክቦ በ250 ሚሊዮን ብር ካፒታል የሕክምና ቁሳቁስን የሚያመርት ሲሆን፣ ከ210 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጥር ይጠበቃል። በ279 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈው ቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የፋማሲዩቲካል ምርቶችን የሚያመርቱ ባለሀብቶች የተሰማሩበት የኢንዱስትሪ ፓርክ እንደሆነ ይታወቃል።

> **አ**ገር በቀል ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በምርት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያሳዩት ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱ የኩባንያዎቹ የማምረት አቅማቸው አድጎ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ተወዳዳሪ የመሆን አቅማቸው ውጤት እያስመዘገበ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የውጭና የአገር ውስጥ ኩባንያዎች በሽርክና የሚሰሩበት የቢዝነስ ሞዴል እድገት እያሳየ እንደሆነም ጠቋሚ ነው

በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሕክምና መሳሪያዎች ፍላጎትና እጥረት አለ። አብዛኛው የሕክምና ቁሳቁስ ከውጭ የሚገባ ነው። ‹‹ኤን ኬ ወርልድ ሜዲካል ኢኪዩፕመንት ማኑፋክቸሪንግ›› የሚያመርታቸው የህክምና ቁሳቁስ አሁን አገሪቱ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የምታስገባቸውና ከፍተኛ ተፈላጊነት ያላቸው ናቸው። ኩባንያው የሕክምና ቁሳቁስን በማምረት ላይ ስለሚሰማራ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች ተክቶ የአገሪቱን ፍላጎት በማሟላትና ምርቶቹን ለውጭ ገበያ አቅርቦ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ረገድ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል። ምርቶቹ በአገር ውስጥ ሲመረቱ ለምርቶቹ ግዢ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ማዳንም ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪም አገሪቱ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት 60 በመቶ የሚሆነውን የመድሃኒትና የሕክምና መሳሪያዎች ፍላጎቶቿን በአገር ውስጥ ለማምረት የያዘችውን እቅድ ለማሳከት የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ ከኮርፖሬሽኑ ጋር ስምምነት የተፈራረሙት ኩባንያዎች ለሥራ እድል ፈጠራ ከሚያበረክቱት አስተዋፅኦ በተጨማሪ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግርን እውን በማድረግ የሚኖራቸው ሚናም የላቀ እንደሚሆን ይናገራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፤ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው የሚያለሙ ኩባንያዎች ለዜጎች የሥራ እድል የመፍጠር ፋይዳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖርና የምርት ተግባራት በቴክኖሎጂ የታገዙ እንዲሆኑ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። በዚህም የምርት ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ እገዛ ያደርጋሉ።

‹‹አገር በቀል ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲገቡ ያስደስታል›› የሚሉት አቶ አክሊሉ፤ ‹‹አገር በቀል ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በምርት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያሳዩት ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱ የኩባንያዎቹ የማምረት አቅማቸው አድጎ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ተወዳዳሪ የመሆን አቅማቸው ውጤት እያስመዘገበ እንደሆነ ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪም የውጭና የአገር ውስጥ ኩባንያዎች በሽርክና (Joint Venture) የሚሰሩበት የቢዝነስ ሞዴል እድገት እያሳየ እንደሆነም ጠቋሚ ነው›› ሲሉ ያብራራሉ።

እንደ አቶ አክሊሉ ማብራሪያ፣ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የጨርቃ ጨርቅ ምርቶችን የሚያመርቱ በርካታ ኩባንያዎች አሉ። ከእነዚህ ኩባንያዎች መካከል በዓለም አቀፍ ደረጃ ስመ ጥር የሆኑ ትልልቅ አምራቾች ይገኛሉ። እነዚህ አምራቾች ክርና ሌሎች ጥሬ እቃዎችን የሚያገኙት ከውጭ ገበያ ነው። ይህ ደግሞ አገሪቱ ካላት ውስን የውጭ ምንዛሬ አንፃር በምርቱም ላይ ሆነ በአገሪቱ ላይ ጫና እንደሚያሳድር ይታወቃል። ‹‹ወርቃ ትሬዲንግ›› የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ግብዓት የሆነውን ክር የሚያመርት በመሆኑ የግብዓት እና የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለማቃለል እንዲሁም ምርቶቹን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ይረዳል።

በሌላ በኩል የ‹‹ኤን ኬ ወርልድ ሜዲካል ኢኪዩፕመንት ማኑፋክቸሪንግ›› ወደ ቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብቶ በምርት ሥራ ላይ መሰማራቱ በኢትዮጵያ ጤናው የተጠበቀ ዜጋ እንዲኖር የተቀመጠው ማኅበራዊ ፖሊሲ እንዲሳካ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው አቶ አክሊሉ ያስረዳሉ።

ከዚህ በተጨማሪም ‹‹የኢንቨስትመንት ዘርፍን ለማሳደግ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ጥራቱን የጠበቀና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ያለው አገልግሎት እየተሰጠ ነው›› የሚሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚው አቶ አክሊሉ ታደሰ፤ የአገር ውስጥና የውጭ ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው እንዲያመርቱ ኮርፖሬሽኑ በትኩረት ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርግ ይናገራሉ። ባለሀብቶች በርካታ ጥቅሞችንና እድሎችን ወደያዙት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ እንዲሰማሩም ጥሪ አቅርበዋል።

ባለሀብቶችን ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለመሳብ በሚደረገው ጥረት ለዘላቂ የአገር ልማትና እድገት አስተማማኝ ዋስትና መሆን የሚችሉትን የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ዐቢይ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል።

የምጣኔ ሀብት ጥናቶች እንደሚያስረዱት፣ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ለዘላቂ የአገር ልማትና እድገት አስተማማኝ ዋስትና መሆን የሚችሉ የልማት አንቀሳቃሾች ናቸው። በአሁኑ ወቅት በምጣኔ ሀብታቸውና በፖለቲካ ተፅዕኗቸው የዓለም ኃያላን የሆኑት አገራት የአገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸውን በመደገፍ ረገድ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል። እነዚህ አገራት ባለሀብቶቻቸውን በማገዝና በመጠበቅ የሰሩት ሥራ የአምራችነት አቅማቸውን አሳድጎ የምጣኔ ሀብት እድገታቸው ዘላቂ እንዲሆን አስችሏቸዋል።

የበለፀጉት አገራት የአገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸውን ቀደም ባሉት ጊዜያት ብቻም ሳይሆን አሁንም ከፍተኛ ድጋፍና ጥበቃ ያደርጉላቸዋል። አገራቱ በፋይናንስ አቅርቦትም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ለባለሀብቶቻቸው የተለየ የድጋፍ መርሃ ግብር አላቸው። የበለጸጉት አገራት ለአገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸው የሚያደርጉት ድጋፍ፣ ገና በማደግ ላይ ያሉ አገራት ከሚያደርጉት ድጋፍ ቢበልጥ እንጂ አያንስም። ለአሁኑ የምጣኔ ሀብት ኃያልነታቸው መሰረት የሆናቸውና ከውጭ ጥገኛነት ያላቀቃቸው የውስጥ አምራችነት አቅማቸው ማደግ እንደሆነ ይታወቃል።

በጂግጂጋ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር እና የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ጥናትና ምርምር ዘርፍ ኃላፊ ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ግርማ፤ ‹‹መንግሥት ኢኮኖሚውን ነፃ አድርጎ ችግሮች ሲያጋጥሙ ድጋፍ/ድጎማ በማድረግ ባለሀብቶችን ማገዝ ይኖርበታል። የግሉ ዘርፍ የኢኮኖሚው ዋነኛ አንቀሳቃሽ ሞተር በመሆኑ ይህን ዘርፍ በተደራጀና ተቋማዊ በሆነ መልኩ መምራትና መደገፍ ይገባል›› ይላሉ።

እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍ ጥረት በብዙ መልኮች ሊገለፅ ይችላል። የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን የሚያበረታቱ ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችን በመቅረፅ፣ ፋይናንስን ጨምሮ ግብዓቶችን በማቅረብ፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦትን በማሟላት እንዲሁም ቢሮክራሲያዊ የአሰራር ውጣ ውረዶችን በማቃለል ለባለሀብቶቹ ድጋፍ ማድረግ ይቻላል። ባለሀብቶቹ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ ከሚኖራቸው ሚና ባሻገር ለዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር፣ ገቢ ምርቶችን በመተካት እና የወጪ ንግድን በመጨመር ትልቅ አስተዋፅዖ ስለሚኖራቸው ይህን ሚናቸውን የበለጠ እንዲያሳድጉ በመንግሥት ድጋፍ መደረግ ይኖርበታል።

በተለይ ኢትዮጵያ በሥራ አጥነትና በዋጋ ንረት እየተፈተነች ባለችበት በአሁኑ ወቅት የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ እጅግ አስፈላጊ ተግባር ነው። መንግሥት ለባለሀብቶቹ የሚያደርገው ድጋፍ ምጣኔ ሀብቱን በማነቃቃት፣ የሥራ እድል በመፍጠር፣ የገቢ ንግድ እቃዎችን በመተካት፣ የወጪ ንግድን በማሳደግ ጥቅል አገራዊ ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴው ዘርፈ ብዙ ለውጥ እንዲኖረው ያደርጋል። የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ አገር በራሷ አምራቾች ላይ እንድትተማመን ያስችላል። ተለዋዋጭ በሆነው የዓለም ፖለቲካ ምክንያት በሚፈጠሩ ችግሮች ከሚከሰት አደጋ ለመዳንም ይረዳል።

ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ፤ ኢኮኖሚያዊ የሆኑትን አብዛኞቹን አስፈላጊ የኢንቨስትመንት ግብዓቶች ባለሀብቶቹ በራሳቸው ለማሟላት ጥረት እንደሚያደርጉ አመልክተው፣ መንግሥት ቢሮክራሲያዊ የአሰራር ውጣ ውረዶችን በማቃለል ረገድ ትልቅ ሚና ሊኖረው እንደሚገባ ይናገራሉ። ለአብነትም መንግሥት አሰልቺ የሆኑ የአሰራር ሰንሰለቶችን በማሳጠርና አገልግሎትን በማቀላጠፍ እንዲሁም የንብረት ጥበቃ በማድረግ ለባለሀብቶቹ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል። በተጨማሪም ባለሀብቶቹ በኢንቨስትመንት ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ ዘላቂ እንዲሆን መንግሥት የኃይል አቅርቦትን፣ የመንገድና የሎጂስቲክስ አገልግሎቶችን ጨምሮ ለሌሎች የመሰረተ ልማት ችግሮችም መፍትሄዎችን ማበጀት ይጠበቅበታል። የውጭ ምንዛሬን በፍትሐዊነት ማቅረብም የመንግሥት ኃላፊነት ነው ይላሉ።

የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና እድሎች አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት አገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ አይደሉም። ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር ለማሳካት አምራች ዘርፉ አሁን ካለው አፈፃፀም በብዙ እጥፍ እንዲጨምርና እንዲሻሻል ማድረግ ያስፈልጋል። የአምራች ዘርፉ እድገት ሊሻሻል የሚችለው ከኢንቨስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ነው። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደግሞ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ተግባራዊ በማድረግ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ናቸው።

መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግሩን ለማሳካት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን አፈፃፀም ማሻሻል ይገባል። ይህም ባለሀብቶች ወደ ፓርኮቹ ገብተው ለማምረት የሚያስችሏቸውን የመሰረተ ልማት ግብዓቶች፣ የሰለጠነ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅርቦት ማሟላትን እንደሚያካትት ሊታወቅ ይገባል። ኢትዮጵያውያን የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ያላቸው ተሳትፎና ድርሻ በየጊዜው እየተሻሻለ እንደመጣ ባይካድም በቂ የሚባል ግን አይደለም። ስለሆነም ለዘላቂ የአገር ልማትና እድገት አስተማማኝ ዋስትና መሆን የሚችሉትን የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

# ጎሜ

# አለማሳወቅ ዋጋ ያስከፍላል

**ምሕረት ሞገስ**

ሰሞኑን የዓለም ዋንጫ እግር ኳስ መኖሩን ተከትሎ ዘውዴ መታፈሪያ፣ ተሰማ መንግስቴ እና ገብረየስ ገብረማሪያም በጊዜ ወደ ቤታቸው በመግባት እግር ኳስ ማየት በመጀመራቸው አብሮ ማምሸት ቀንሰዋል። ትናንትና ግን ጨዋታው ባለመኖሩ ተደዋውለው ተገናኙ። አመሻሽ ላይ ገብረየስ እንደልማዱ ቀድሞ በግሮሰሪው ተገኝቶ ያላበው ቢራ እየተጎነጨና እያጣጣመ ጠበቃቸው። ዘውዴም ብዙ ሳይቆይ በቦታው ተከሰተ። ተሰማ ግን ግማሽ ሰዓት አስጠብቋቸዋል።

ስለሰሞኑ እግር ኳስ ካወሩ በኋላ ፋይዳው ላይ መከራከር ጀመሩ። ዘውዴ እግር ኳስ አገራዊ ስሜትን ለማምጣት እና አንድነትን ለመፍጠር ብቻ ሳይሆን ዓለምን አንድ ለማድረግም ትልቅ መሳሪያ ነው ሲል፤ ገብረየስ ግን ዓለምን አንድ ማድረግ የማይታሰብ ነው፤ እንዳውም ከመዝናኛነት ያለፈ ፋይዳ የለውም ሲል ተከራከረ። ተሰማ ሁለቱንም ለማስማማት ሳይሆን የሚያምንበትን እንደሚናገር ገልፆ፤ ለመዝናናት እንደሚያገለግል ግን ደግሞ ዓለምን አንድ ለማድረግ ሳይሆን አገራዊ ስሜትን እና አንድነትን ለማምጣት ትልቅ መሳሪያ ነው የሚል እምነት እንዳለው ጠቆም አደረገ። አያይዞ ግን ሁልጊዜ ዘውዴ ስለአንድነት አብዝቶ መናገሩ ልዩነት መኖሩን እንዳያስረሳ ስጋት እንዳለበትም አብራራ።

ዘውዴ ‹‹እርግጥ ነው። ሰው ከሰው ይለያያል። ሰው ከሰው እንደየደረጃው አንድ የሚያደርገው ነገር ደግሞ ይበዛል። በዓለም ያለው ሰው በሙሉ ይበላል፤ ይጠጣል። ሳይበላ ሳይጠጣ የሚኖር የለም። ይህ የዓለም ህዝብን አንድ ያደርጋል። በተቃራኒው ደግሞ የዓለም ሕዝብን እያንዳንዱን ሰው የሚያለያይ ነገር አለው። ምክንያቱም የእያንዳንዱ ሰው የዓይን ብሌንም ሆነ የጣት አሻራ የተለያየ ነው። ሰዎች በቀለማቸው በመልካቸውም ሆነ በአስተሳሰባቸው የተለያዩ ናቸው። ይሔ ምንም ጥርጥር የለውም። ልዩነታችንን አንዱ ከሌላው ለመለየት በሚያስፈልግበት ጊዜ እንገልጸዋለን። በተረፈ ግን ዓለም እንደሚስማማው ሰዎች ሁሉ ነፃ እና እኩል ናቸው። ስለነፃነት እና እኩልነት ስናስብም ሆነ ስንናገር ሰዎች ሁሉ አንድ ናቸው በማለት እንስማማለን።›› አለ።

ተሰማ በዘውዴ ሃሳብ ፈገግ አለ፤ ‹‹አንተ ስለዓለም ሕዝብ እኩልነት፣ ነፃነት እና አንድነት ትናገራለህ። እኛ የአገርን አንድነት ለማምጣት ተራራ ሆኖብናል።›› አለ። ዘውዴ በበኩሉ ‹‹በጥባጭ ካለ በሰላም ለመኖር ችግር ማጋጠሙ የማይቀር ነው። ‹በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ውሀ ይጠጣል› ይባል አይደል? ስለአንድነት ደጋግመን የምንናገረው ወደን አይደለም። ወይም የራሳችን የምንለያይባቸው ነገሮች መኖራቸውን ዘንግተን አይደለም። ስለዓለም አንድ መሆን መግለፅ ብዙም ትርጉም ላይሰጠን፤ ወይም ዓለም አንድ መሆን አለበት ብለን ልንከራከርም ሆነ ላንከራከር እንችላለን። ነገር ግን ስለአገር አንድነት የምንለፈልፈው ኢትዮጵያ እንዳትፈርስ እንጠብቃት ብለን ነው።

ነገር ግን ኢትዮጵያ እንድትፈርስ ክፍተታችንን ተጠቅመው እንደ አይጥ ጉድጓድ ውስጥ እየተሽሎከለኩ ተግተው የሚሰሩ አሉ። ወደድንም ጠላንም፤ ባለማወቅም ሆነ እያወቅን ለማመን ብናመነታም ልዩነታችንን በማጉላት ላይ የሚሠሩ አሉ። ልዩነታችን መለያያችን ሳይሆን ውበታችን መሆኑን ማሳየት አለብን። እነሱ የሚያደፈርሱትን የኢትዮጵያ አንድነት ለማጽናት ስለኢትዮጵያ አንድነት ደጋግመን እንገልፃለን። ስለልዩነታችንማ እነርሱ በደንብ ደጋግመው በተለያየ መንገድ እየገለፁ ስለሚያስደነብሩን ስለልዩነታችን ደጋግሞ ማንሳት ተገቢ አይደለም። ልዩነታችን ውበት ጌጥ መሆኑን ግን ማሳየት ያስፈልጋል።

ነገሩ የኢትዮጵያ ምሁራኖችም ሆኑ አንዳንዴም የመንግስት ባለስልጣኖች ‹ሞኝ ለጠበቃው ሚስጥር ይሸሽጋል› እንደሚባለው ለአገር ጠበቃ ለሆነው ሕዝብ ሁሉን ነገር ግልፅ አድርገው በማሳወቅ የጋራ ዓላማ ይዞ አገር ከማቆም ይልቅ ሞኝ ችግሩን ለሚያቃልልለት ሰው እንደማይናገረው እና ችግር ላይ እንደሚወድቀው ሁሉ እነርሱም ስለኢትዮጵያ ጠላቶች በግልፅ በሚገባው ልክ ለሕዝብ ባለመናገራቸው ችግር ያጋጥማል።

ከ120 ሚሊየን ያላነሰ ሕዝብ ያላትን ለዛውም 70 በመቶ የሚሆነው መሥራት የሚችል ሕዝብ ያላትን ኢትዮጵያን፣ በባህል፣ በቋንቋ እና አንዳንዴም በዘር ሃረግ ሳይቀር ከጎረቤቶቿ ከኬንያም ሆነ ከሱዳን፣ ከኤርትራም ሆነ ከጅቡቲ፣ ከደቡብ ሱዳን ጋርም ሆነ ከሶማሌያ ጋር የምትተሳሰረውን ኢትዮጵያ፤ ምስራቅ አፍሪካን ጠቅልላ ነገ የዓለም ታላቅ አገር ሆና ልዕለ ሃያል እንዳትሆን አጥብቀው የሚሰሩ አይጠፉም።

በተጨማሪ ኢትዮጵያ የወደፊት ስጋታቸው ናት ሲባል የውሃ በረከትን የተጎናፀፈች ሕይወት የሆነውን ውሃ ለጎረቤቶቿ አሳልፋ የምትሰጥ ነች። ለጎረቤት አገራት በሙሉ ውሃዋን እያሳለፈች ትቸራለች። ይህ ለጋስነቷ ከአገራቱ ጋር ያስተሳስራታል። ለሱዳን አባይን፣ ለኤርትራ ተከዜን፣ ለኬንያ ቱርካናን፣ ለጅቡቲ አዋሽን መስጠቷ አገራቱ እንደእናታቸው እንዲያዩዋት ያስገድዳቸዋል። በሚደንቅ መልኩ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በብሔር እና በቋንቋ ከእነዚሁ አገራት ጋር ትተሳሰራለች። በተጨማሪ በታሪክ በቀኝ ባለመገዛት እና ለቀኝ ተገዢዎች ‹እምቢኝ› እንዲሉ ምሳሌ መሆኗ እና ወደፊትም በዚሁ መልኩ ሌሎቹንም ለተዘዋዋሪ ቀኝ ግዛት አንበረከክም እንዲሉ መንገድ ትከፍታለች ብለው የኢትዮጵያ መኖር እና ማደግ ያሳስባቸዋል።

‹‹ኢትዮጵያውያን ግን ዳሩ ሲሄድ መሃሉ ዳር እንደሚሆን ረስተን፤ ዳር ላለው ጥንቃቄ ካልተደረገ የመሃሉ ላይ እንከን እንደሚፈጠር ዘንግተን፤ ለመሃሉ የዳሩ ጥንካሬ ወሳኝነት እንዳለው በውል ሳናስብ፣ ዳር ላለው ምንም ሳንሠራ ኢትዮጵያዊነት እንደሚቀጥል እርግጠኛ ሆነናል። መሃል ያለው ኦሮሞ፣ ጉራጌ፣ ትግሬ፣ አማራ … ማንም ሆነ ማን ብቻውን ‹ኢትዮጵያ ነኝ› ቢልም ብቻውን ከሆነ አማራ ወይም ኦሮሞ እንጂ ኢትዮጵያን መሆን አይችልም። ይሔንን ዘንግተነዋል። በማለት ዘውዴ ረዥም ንግግሩን የበለጠ እየለጠጠ ለማስረዘም ሲሞክር ተሰማ አቋረጠው።

‹‹ለማለት የፈለግከው አልገባኝም። ምን ማለትህ ነው?›› ሲል ተሰማ ዘውዴን ጠየቀ። ዘውዴም በደፈናው ‹‹ምከረው ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው›› ማለቴ ነው። አለው። ተሰማ የበለጠ ግራ ተጋባ። ገብረየስም የዘውዴ ንግግር ግልፅ የሆነለት አይመስልም። ገብረየስ በመጠኑ የተረዳው ኢትዮጵያን ለሁሉም የምትመች አገር እንድትሆን ምሁራን በሙያቸው ሰፊ ስራ ሊሰሩ ይገባል። በጥናትና ምርምሩ፣ ለችግሮች መፍትሄ በማመላከት እንጂ እነሱ የችግሩ አካል መሆን የለባቸውም። ችግር አባባሽ መሆን አይገባቸውም። አሁን አንዳንዱ ከመህይም አስተሳሰብ የባሰ ሀሳበ ያለው ነው። ግን ድፍረት አይሁንብኝ እንጂ የስም ምሁራን አጋጥመውኛል። ዘውዴ ወደ ኋላ የተነገረው ግን በደንብ አልገባውም።

ዘውዴ በበኩሉ ‹‹በየዘመኑ በተለያየ መልኩ በደል ይኖራል። በነገስታቱ ጊዜ ባላባቶች ደሃው ላይ ሲጨክኑ ‹ደሃ የሚለብሰው እንጂ የሚከፍለው አያጣም› እያሉ በብዛት ያስገብሩ ነበር አሉ። ደሃ ቢጥርም ቢለፋም የሚከፍለውን ሲቆልሉበት ቅሬታ እየተሰማው ቢቆይም ፈርቶም ቢሆን ከመክፈል ወደኋላ አይልም ነበር። ‹ትናንት ጦሙን ያደረ ማን ነው?› ሲባል ‹እኔ ነኝ› ለሚል መልስ የሚሰጠው ‹ዛሬም ድገም ተብለሃል› ተብሎ ተመሳሳይ ችግር እንዲያጋጥመው ይደረግ ነበር አሉ። ዛሬም በኢትዮጵያ ያለው ተመሳሳይ ነው።

**ኢትዮጵያ እንድትፈርስ ክፍተታችንን ተጠቅመው እንደ አይጥ ጉድጓድ ውስጥ እየተሽሎከለኩ ተግተው የሚሰሩ አሉ። ወደድንም ጠላንም፤ ባለማወቅም ሆነ እያወቅን ለማመን ብናመነታም ልዩነታችንን በማጉላት ላይ የሚሠሩ አሉ። ልዩነታችን መለያያችን ሳይሆን ውበታችን መሆኑን ማሳየት ግን አለብን**

ኢትዮጵያውያን ዛሬም በደህነት ውስጥ እየማቀቅን ነው። ዳኛ ገንዘቡን ተቀማ እንደሚባለው፤ ለሌላው መትረፍ የሚችል ሕዝብ ለራሱ ሳይሆን ቀርቷል። በምሁራኖችም በመንግስትም በኩል ነገር ከልኩ ላያልፍ ቁምነገርን መልቀቃቸው ያስከፋል። በስሜት ወይም በይሉንታ ፈርቶ ሁሉን ከማሳወቅ መገታት ያሳዝናል። ትክክል ሊሆኑ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች ቢኖሩም ከጠላት ቀድሞ በመንቃት ምቀኛ አታሳጣኝ እያሉ፤ ምቀኛ የጠላውን የጎዳ መስሎት ተንኮል ሲሠራ ሳያስበው የሚመቀኘውን እንደሚጠቅመው ሁሉ ኢትዮጵያን ታሪካዊ ጠላቶች መኖራቸውን በውል በማሳወቅ፤ አገር ለመጉዳት እየሰሩ ያሉትን በማጋለጥ የአገርን አንድነት ከማጠናከር ወደኋላ ማለት ሞኝነት ነው።

ራሳቸው አጥፍተው ሌላውን እንደጥፋተኛ አስመስለው የሚናገሩ ሃላፊዎች፤ በብዙ መልኩ ስለአገሪቱ ታሪክ ብቻ ሳይሆን አሁን ስላለው የዓለምም ሆነ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ስለኢትዮጵያውያን ስነ ልቦና፤ ወደፊት ለማደግ ስለሚቻልበት መንገድ ያለውን የመርፌ ቀዳዳ የሚያህል ዕድል መጠቀም ሲገባ ወደኋላ ማለት ‹ ማዕረገ ቢስ ራቱ ገሚስ › እንደሚባለው ይሆንባቸዋል።

ምክንያቱም ከሞት በኋላ የሚፃፍ ታሪክ እንዲኖረው ዕድሉን ያገኘ ሰው የተሰጠውን ዕድል በትክክል የማይጠቀም ከሆነ እንደውም በተሰጠው ዕድል ሳቢያ ችግር ያጋጥመዋል። መቼም ጆሮ አይሰጥምና በብዙ መልኩ ስለአንዳንዶች ጥሩውንም ሆነ መጥፎውን እየሰማን ነው። እናም የጊዜው ዕድለኞች ከተቀበሉን በተቻለን መጠን እንመክራለን። ካልሰሙን ግን ችግር ሊያስተምራቸው ስለሚችል እንተዋቸዋለን። ‹ደንቆሮ የሰማ ዕለት ያብዳል› እንደሚባለው እኛ የነገርናቸውን ካልሰሙ፤ ሰው ሰምቶት የማያውቅ የሚያበሳጭ ነገር ሲያጋጥማቸው በጣም መናደዳቸው አይቀርም። እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው ቢነሱም ጊዜው ያልፋል። ምን ያምጣ ድሃ ምን ይግዛ ውሃ ብለው የናቁት ህዝብ በደሉን ስለሚያስብ እርሱም በተራው አልሰማም ማለት ሲጀምር የቤት ሥራውን በአግባቡ ያልሰራው ኃላፊ፤ እንኳን ከሞት በኋላ መልካም ታሪኩ ሊፃፍና ሃውልት ሊቆምለት ቀርቶ ተራ ሆኖ መኖር እንደሰማይ ይርቀበታልና ሁላችንም ከወዲሁ ብናስብ ይሻላል።›› ሲል ዘውዴ የዕለቱን ማሳሰቢያውን ተናግሮ እንደልማዱ የጠጣበትን ሳይከፍል ወደቤቱ ለመሔድ ሲነሳ ተሰማ እጁን ጎትቶ ወንበሩ ላይ አስቀመጠው።

ተሰማ ለዘውዴ፤ ‹‹መጨረሻ ላይ በአንድ ዓረፍተ ነገር ይሔንን ሁሉ የተናገርከው ምን ለማለት ፈልገህ ነው? ሳታወሳስብ በግልፅ ንገረኝ። ከዛ የዕለቱን የጠጣህበትን ምንም ሳላንገራግር እዘጋዋለሁ ›› አለው። ዘውዴ ቆጣ ብሎ ፤ ‹‹ ወደህ ነው፤ ሕዝብ የሚበላውን እና የሚጠጣውን ማሟላት ባትችሉም በስሱም ቢሆን መከፈል ግዴታችሁ ነው።›› አለ። በድጋሚ ንግግሩን ቀጥሎ ‹‹ ማለት የፈለግኩት መንግስትም ሆነ ምሁራኖቻችን የኢትዮጵያ ጠላቶች ኢትዮጵያን ለማጥፋት ምን ይህል እየተጉ መሆኑን እያወቁ፤ ካወቁም በኋላ ደግሞ ለሕዝብ በትክክል አለመግለፃቸው አደጋ አለው የሚል ነው። ሕዝብ ቢያውቅ ከጎናችሁ ሆኖ ይደግፋችሁ፤ ያለበለዚያ ሕዝብ ያጠፋችኋል ለማለት ነው። ስለኢትዮጵያ ጠላቶች ዓላማ በዝርዝር ማወቅ ከፈለግክ ደግሞ ሰሞኑን የዓለም ዋንጫ እግር ኳስን ስትመለከት በነበረው ሰዓት አንብብበት።›› ብሎ ዘውዴ ከግሮሰሪ ወጣ።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# ሙዚቃና ሰው ወደ ሰዋሰው

ዋሰልኝ አየለ

የሙዚቃ ታሪክ ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር የተቆራኘ ነው። ብዙ ጊዜ የሚነገርለት ታሪክ ከሸክላ ዘመን በኋላ ያለው ቢሆንም ሙዚቃ ግን ከሰዎች የዋሻ ውስጥ ኑሮ ጀምሮ በኢመደበኛ ደረጃ ሲንጎራጎር የቆየ ነው።

በሸክላ መታተም ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ ያለው የሙዚቃ ታሪክ ግን መደበኛ የሙዚቃ አይነት ስለሆነ ብዙ ተብሎለታል። የሰው ልጅ የሥልጣኔ ደረጃ እያደገ እና እየዘመነ በመጣ ቁጥር የሙዚቃ ማጫወቻ አይነቶችም እየተለወጡና እያደጉ መጡ።

አሁን ላይ ባለው ወጣት ትውልድ የልጅነት ትዝታ ያለው ደግሞ ካሴት ነው። የካሴት ቅጂ የተጀመረው በአውሮፓ አገራት ውስጥ በ1960ዎቹ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። በእነዚህ ዓመታት የነበሩ የኢትዮጵያ ሙዚቃዎች የሚታወቁት በሸክላ ሥራዎች ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የካሴት ቅጂ የተጀመረበትን ትክክለኛ ጊዜ ባናገኝም ከ1970ዎቹ እና 1980ዎቹ ጀምሮ ግን የካሴት ሥራዎች አሉ። በተለይም በአሁኑ ወጣት ትውልድ ዘንድ ከፍተኛ የልጅነት ትዝታ ያላቸው ደግሞ የ1990ዎቹ የሙዚቃ ሥራዎች የሚታወቁት በካሴት ነው።

የሰው ልጅ የሥልጣኔ ደረጃ አይነቱንና መልኩን እየቀየረ መሄዱን ቀጥሏል። ብዙ ባህላዊና ልማዳዊ አሰራሮች በዘመናዊና ረቂቅ ቴክኖሎጂዎች ተተኩ። ከእነዚህም አንዱ የሙዚቃው ዘርፍ ነው። በአገራችን በተለይም ከሚሊኒየም በኋላ የሲዲ እና ዲ ቪ ዲ ማጫዎቻዎች ፋሽን ሆነው መጡ።

እነዚህ ማጫወቻዎች ከካሴት ጋር ጎን ለጎን አብረው የተወሰኑ ጊዜያት ቢሄዱም የካሴት ነገር ግን ልክ እንደ ሸክላ ሁሉ እየተረሳ መጣ። እነዚህን የሲዲ እና ዲ ቪ ዲ ማጫወቻዎችን በቴሌቭዥን ማጫወት ተለመደ። በድምጽ ብቻ ይሰሙ የነበሩ ዘፈኖችን በተንቀሳቃሽ ምስል (ቪዲዮ) ማየት ጭምር ተለመደ። አዳዲስ ሙዚቃዎች ሲሰሩ በቪዲዮ ጭምር እየሆነ መጣ።

ቴክኖሎጂ ወለድ የሆኑት እንደ ፍላሽ እና የእጅ ስልኮች ሚሞሪ ካርድ ደግሞ ተጨማሪ የሙዚቃ ማጫወቻዎች ሆነው መጡ። ዳሩ ግን እነዚህ ነገሮች ለሙዚቃው ኢንዱስትሪ ደግሞ ትልቅ ፈተና አስከተሉ። ‹‹ፍላሽ ክላሽ›› እስከሚባል ድረስ የፈጠራ ሥራዎችን በሕገ ወጥ መንገድ በማባዛት ለሌብነት በር ከፈቱ።

የቴክኖሎጂው ዕድገትና ለውጥ ቀጥሏል። በአገራችን ከ10 ዓመታት በፊት ጀምሮ ደግሞ የ‹‹ዩ ትዩብ›› አማራጮች ሌላ የሙዚቃ መስሚያ አማራጭ ሆነው መጡ። በቀጥታ ከበይነ መረቡ ዓለም ላይ በማውረድ ሰዎች በራሳቸው የእጅ ስልኮች ወይም በቴሌቭዥን እና በሌሎች የማጫዎቻ አማራጮች መስማት ጀመሩ።

በእነዚህ ሁሉ የቴክኖሎጂ ቅብብሎሽ ውስጥ ሙዚቃዎችን ለማግኘትና ለመስማት ምቹ ሁኔታ ቢፈጠርም ባለቤቶችን ግን አመድ አፋሽ አደረገ። የሙዚቃ ባለሙያው ከሥራው ተጠቃሚ መሆን አልቻለም።

ይህን ችግር ለመቅረፍ ነው እንግዲህ የሙዚቃ ባለሙዎች አንድ ዘዴ የፈጠሩ። ይሄውም የራሱ የሙዚቃ መተግበሪያ መፍጠር ማለት ነው። ይህ የሙዚቃ የሞባይል መተግበሪያ ‹‹ሰዋሰው›› የሚባል ሲሆን ባለፈው ሐሙስ ኅዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም በስካይላይት ሆቴል ከሙዚቃ ባለሙያዎች ጋር መሥራት የሚያስችለውን ስምምነት ተፈራርሟል።

አንጋፋዋን ድምጻዊት ማሪቱ ለገሰን ጨምሮ፤ ቴዎድሮስ ካሳሁን፣ ካሙዙ ካሳ፣ አብነት አጎናፍር፣ ግርማ ተፈራ፣ ሔኖክ አበበ፣ ራሄል ጌቱ፣ ያሙሉ ሞላ፣ ለምለም ኃይለሚካኤል፣ ብሌን ዮሴፍ፣ ዘሩባቤል ሞላ እና ሌሎች ከ80 በላይ የሚሆኑ አንጋፋና ወጣት የሙዚቃ ባለሙያዎች ከሰዋሰው መልቲ ሚዲያ ጋር ለመስራት የስምምነት ሰነድ ተፈራርመዋል።

ሰዋሰው መልቲ ሚዲያ ሙዚቃን በቀላሉ በኦንላይን ለመገበያት የሚያስችል የመተግበሪያ ዘዴ




ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

ቴክኖሎጂው በፈጠረው ዕድል በሙዚቃ ሥራው ውስጥ ለተሳተፉ ሰዎች ዕውቅና ይሰጣል፣

ሲሆን ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት 300 ሚሊዮን ብር ካፒታል ይዞ ነው ሥራ የጀመረው።

በዕለቱ ባለሙያዎቹ በጋራ በሰጡት መግለጫ እንደተነገረው፤ መተግበሪያው የኢትዮጵያ ሙዚቃዎች ድንበር ተሻጋሪ ታዳሚ እንዲያገኙ ያደርጋል። ባለተሰጥኦዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የሙዚቃ ሥራዎች የአከፋፋይ እጥረት ሳይገድባቸው በየትኛውም ቦታ እንዲደመጡ ያደርጋል።

በሙዚቃ ሥራዎች ግብይት ላይ የሚሰራው ሰዋሰው መልቲ ሚዲያ፤ ተሰርተው የተጠናቀቁ ሙዚቃዎችን ገዝቶ በተመጣጣኝ ዋጋ ለታዳሚዎች ከማድረስ በተጨማሪ ባለተሰጥኦዎች ችሎታቸውን የሚያወጡበት ዕድል ይፈጥራል።

ሰዋሰው መተግበሪያ ሕገ ወጥ ቅጂ ይበዛበት የነበረውን የሙዚቃ ኢንዱስትሪ የባለተሰጥኦዎችን የባለቤትነት መብት ባስከበረ የቴክኖሎጂ አሰራር ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው ነው ተብሏል። ይሄውም፤ ለባለፈጠራዎቹ ጠቀም ያለ ክፍያ በመክፈል ሙዚቃውን ራሱ ይሸጣል ማለት ነው። ባለፈጠራዎቹ ውል ከተፈራረሙ በኋላ ሥራቸውን ማስረከብ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ አከሰረውም አተረፈውም ሥራው የሰዋሰው ነው።

የሰዋሰው መልቲ ሚዲያ የሙዚቃ ዲፓርትመት ኃላፊ ሀብቱ ነጋሽ እንደገለጸው፤ ሰዋሰው መልቲ ሚዲያ የሙዚቃ ስራዎችን ሲገዛ ሁለት አይነት አሰራሮችን ይከተላል። አንደኛው፤ ታዋቂና የራሳቸውን ስራ ራሳቸው ወጪውን ችለው ሙሉ አልበም የሚሰሩ ድምጻውያን ሥራ የሚቀርብበት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ይህ አቅም የሌላቸው ነገር ግን የሙዚቃው ተሰጥኦና ችሎታው ያላቸውን ወጣት ድምጻውያን ከባለሙያ ጋር በማገናኘት፣ የግጥምንና ዜማ እንዲሁም ሌሎች ወጪዎችን በመሸፈን ሙሉ አልበም የሚሰሩበትን መንገድ ያመቻቻል።

ሐብቱ ነጋሽ ለቁም ነገር መጽሔት በሰጠው መረጃ፤ ከእያንዳንዱ ድምጻዊ ጋር የሚደረገው ስምምነት እንደ አርቲስቱ ይለያያል። አርቲስቶች ከአልበማቸው ጋር አንድ የሙዚቃ ኮንሰርት እንዲሰሩ ስምምነት የሚያደርጉ ሲሆን ከአልበሙ ላይ ሶስት ዘፈኖችን ክሊፕ መስራት እንደ አንድ መስፈርት ተቀምጧል፤ የክሊፑን ወጪ በሰዋሰው አልያም በአርቲስቱ የሚሸፈን ሲሆን በሰዋሰው የዩቲዩብ ቻናል ላይ ብቻ ነው የሚጫነው።

የፊርማ ስምምነቱ በተደረገበት ዕለት ባለሙያዎቹ ለጋዜጠኞች በጋራ በሰጡት መግለጫ፤ ስምምነት ከተደረገ በኋላ ሙሉ ኃላፊነቱን ወስዶ የሚሰራው ሰዋሰው ነው። ባለሙያዎቹ ሥራቸውን ለሰዋሰው አንዴ ከሸጡ በኋላ ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ከገቢው ላይ መብት መጠየቅ አይችሉም። ሰዋሰው ሙሉ ወጪውን ሸፍኖ የገዛ በመሆኑ አርቲስቶቹ በራሳቸው የዩቲዩብ ቻናል ላይም ሆነ የሮያሊቲ ክፍያ በሚሰበሰብበት የብሮድካስት ሚዲያ ላይ ስራዎቻቸውን አሳልፈው የመስጠት መብት አይኖራቸውም።

ሰዋሰው የሙዚቀኞቹን ስራ አድማጭ ጋር ለማድረስ የማስተዋወቅ ስራውን ሙሉ ኃላፊነት ወስዶ የሚሰራ ሲሆን ከቅጂና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማህበር አማካይነት የሚሰበሰበው የሮያሊቲ ክፍያ አዋጁ ለፕሮውዲውሰሩ የሚፈቅደውን መብት ጨምሮ ለ5 ዓመታት ማስተዳደር የሰዋሰው መብት ይሆናል ማለት ነው።

በዚሁ ዕለት (ኅዳር 29 ቀን ማለት ነው) አሥር ድምፃውያን የተሳተፉበት ‹‹ሻኩራ›› የተሰኘ አልበም በሰዋሰው መልቲ ሚዲያ ቀርቦ ተመርቋል።

በዚህ አልበም ውስጥ፤ ጃሉድ አወል፣ ዘቢባ ግርማ፣ ራስ ዳጊ፣ ኒና ግርማ፣ ዳግማዊ ታምራትን ጨምሮ አሥር አርቲስቶች የተሳተፉበት አልበም ተመርቋል።

በሙዚቃ አቀናባሪና ፕሮዲውሰር ካሙዙ ካሳ የተዘጋጀው ‹‹ሻኩራ›› የተሰኘው ይህ አልበም በዕለቱ ተለቋል። የሙዚቃ አቀናባሪው ካሙዙ ካሳ በዕለቱ እንደተናገረው፤ አልበሙ ወጣት ድምፃውያን የተሳተፉበትና ዳንሶል፣ ሬጌና ሌሎችም የሙዚቃ ሥልቶች ያካተተ ነው።

ይህ የሙዚቃ ባለሙያዎች የፊርማ ስምምነት መደረግ ለአንጋፋ ድምጻውያን ሥራዎችም እንደገና ዕድል ፈጥሯል። ዝርዝሩ ወደፊት ይነገራል ቢሉም የተወዳጇ ድምጻዊት ማሪቱ ለገሠ ኮንሰርት እንደሚዘጋጅም ሰዋሰው መልቲ ሚዲያ በዕለቱ አሳውቋል።

ከ23 ዓመታት በኋላ ወደ አገሯ ትገባለች ተብሎ የምትጠበቀው አንጋፋዋ ድምፃዊት ማሪቱ ለገሠ በአራት ከተሞች ሥራዎቿን እንደምታቀርብ ነው የተነገረው። አቶ ሀብቱ ነጋሽ በዕለቱ እንደተናገሩት፣ አንጋፋዋ ድምፃዊ ማሪቱ ለገሠ በቅርብ ቀናት ወደ አገሯ ትገባለች። ከ23 ዓመታት በኋላ ወደ አገሯ የምትመጣው ማሪቱ፤ በደሴ፣ በጎንደር፣ በባህር ዳርና በአዲስ አበባ ከተሞች ሥራዎቿን ታቀርባለች።

በነገራችን ላይ ሰዋሰው መልቲ ሚዲያ የሙዚቃ ሥራዎችን የሚገዛው በአልበም ደረጃ ያሉትን ነው። ነጠላ ዜማን እንደማያበረታታ በዕለቱ ተነግሯል። በሌላ በኩል ደግሞ የሙዚቃው ይዘቶችም እንደሚታዩ ነው በመግለጫው የተናገሩት።

ሰዋሰው መልቲ ሚዲያ፤ ግጭትን የሚፈጥሩ እና ጥላቻን የሚሰብክ መልዕክት ያላቸው ዘፈኖች ያሉበትን አልበም አይገዛም። ፍቅርና አንድነትን እንዲሁም አገራዊ መልዕክት ያላቸውን ዘፈኖች ነው የሚገዛው ተብሏል።

ሰዋሰው መልቲ ሚዲያ የሰው ልጅ የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ደረጃ ታሳቢ በማድረግ ‹‹ሙዚቃ ድሮ ቀረ›› እንዳይባል የአሁኑም ትውልድ የራሱን አሻራ ሰንዶ የሚያስቀምጥበት ዓውድ ፈጥሯል። በፍላሽ እና የእጅ ስልኮች ሚሞሪ ካርድ ላይ የባለሙያዎችን ታሪክ አናገኝም ነበር። የካሴት ዘመን ላይ የዘፋኙ ስምና ፎቶ፣ የዜማና ግጥም ደራሲ፣ አቃናባሪ፣ በአጠቃላይ በሥራው ውስጥ የተሳተፉ ሰዎች እና የእያንዳንዱ ዘፈን ርዕሶ ተፅፈው በካሴቱ ማቀፊያ ውስጥ ይቀመጡ ነበር።

ሰዋሰው መተግበሪያ ይህን ማንነት ሳይለቅ ቴክኖሎጂው በፈጠረው ዕድል በሙዚቃ ሥራው ውስጥ ለተሳተፉ ሰዎች ዕውቅና ይሰጣል። በአጭር ቪዲዮም ራሳቸው ማብራሪያ ይሰጣሉ። በጽሑፍ እና በምስልም ይቀመጣል።

በአጠቃላይ መተግበሪያው የሰው ልጅ የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ዘመን ታሳቢ በማድረግ የሙዚቃ ትዝታን ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ፣ ዕድሉን ላላገኙ ባለተሰጥኦዎች ከባለሙያ ጋር የሚያገናኝ እና አድማጩንም ተደብቀው ከሚቀሩ ሥራዎች ጋር የሚያገናኝ ስለሚሆን ተጠናክረው ይቀጥሉ እንላለን።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ጨለማውን ወደ ብርሃን የለወጠች ወጣት

**ሰሳማዊት ውቤ**

መሰለች ጃናቶ የስምንተኛ ክፍል ሞዴል ፈተናን ለመፈተን በክፍል ውስጥ ተገኝታለች። ሆኖም ሞዴል ፈተናውን እየሰራች ባለችበት ቅጽበት የዓይኗ ብርሃን ድንገት ድርግም አለ። በጨለማ ውስጥ ተዋጠች።

ይህንን ሁኔታ እንኳን እሷ ጓደኞቿ አላመኑም። ትምህርት ቤት በራሷ ሄዳ በመሪ ስትመለስ ቤተሰቦቿ ተደናገሩ። ክፉኛም ደነገጡ። ያላቸው አማራጭ ሆስፒታል መውሰድ ነበረና የተለያየ ሆስፒታል ወስደው አስመረመሯት። ከአርባ ምንጭ አልፈውም በአገሪቱ ያሉትን ሆስፒታሎች አዳረሱ።

መሰለች ጃናቶ በድንገት አይኗ ሲጠፋ አመቱ 2005 ነበር። እሷም የ20 ዓመት ወጣት ነበረች። መሰለች ጎበዝ ተማሪ ነበረች። ደብል በመምታትም ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው በማለፍ ትታወቃለች። ሆኖም የአይን ብርሃን በድንገት መጨለም ተስፋዋን አብሮ አለጨለመው። ሕይወቷ ባልታሰበ መንገድ ተቀየረ።

‹‹የእኔ ብርሃን መጨለም ሕይወቴን አመሰቃቀለው። ግራ ገባኝ። የአይኔን ብርሃን ለመመለስ ተንከራተትኩ። ሆኖም የትኛውም ሆስፒታል ብርሃኔን ሊመልስልኝ አልቻለም›› ስትልም መፍትሄ ሳታገኝ ወደ ቤቷ መመለሷን ታወሳለች። ዓይነስውር በመሆኗ ትምህርቷ ተቋረጠ። ስትዘጋጅበት የከረመችው ክልላዊውን የስምንተኛ ክፍል ፈተናም መውሰድ አልቻለችም። ትምህርት ቤት መሄድ ቀረና መሰለች ውሎዋ ቤት ቁጭ ማለት ሆነ።

‹‹ጓደኞቼ ትምህርት ቤት ሲሄዱ እኔ ዓይነስውር በመሆኔ ምክንያት እቤት ውስጥ በመዋሌ እያለቀስኩ ነበር ጊዜዬን የማሳልፈው። በጣምም አዝን ነበር›› የምትለው መሰለች ዓመታትን በዚህ ጨለማ ውስጥ መኖር በእጅጉ እንዳማረራትም አልሸሸገችንም። በሕይወት የመኖር ተስፋዋም ተሟጠጠ።

ችግር ሲመጣ እየደራረበ ነው እንደሚባለው መሰለች ብርሃኗን ባጣች ማግስት ሁለቱንም ወላጆቿን በተከታታይ በሞት ተነጠቀች። የምትይዘውን የምትጨብጠውን አጣች። ሰማይና ምድሩ ተደፋባት። በወቅቱ የነበራት ጭላጭ ተስፋም ከውስጧ ተኖ ሲጠፋ ተሰማት። በተደጋጋሚም ራሷን የማጥፋት ሙከራ አደረገች። ሆኖም አልተሳካላትም።

ሕይወት ቀጠለ። ለራሷ ብቻም ሳይሆን ለሁለት ወንድሞቿ መኖር እንዳለባት አመነች። ከሁለት ወንድሞቿ ጋር መኖሯን ቀጠለች። ሴት በመሆኗ የቤቱ ኃላፊነትም በእሷ ጫንቃ ላይ ወደቀ።

መሰለች ቀጥላለች። ‹‹ሕይወት እየመረረኝ ስለመጣ ዕድሌን አሁንም በእጅጉ ከማማረር አልዳንኩም። በዚህ ወቅትም አልቀስ ነበር። ሕይወቴን ለማጥፋት የማደርገውንም ሙከራ አላቆምኩም ነበር ›› ትላለች በወቅቱ ነበረውን ሁኔታ ስታስታውስ። በዚህ ጨለማ ሰዓት አብዝታ በአቅራቢያ ያለ ቤተክርስቲያን ትሄድ ነበር ለራሷም ፀሎት ትፀልያለች። ለእሷም ሰዎች ይፀልዩላት ነበር።

በዚህ ወቅት ነበር አቶ ዘለቀ ከፋሞን ያገኘቻቸው። ዕውነት ለመናገር ለፀሎት ቤተክርስቲያን መሄዴና ከሰው መገናኘቷ ወጣቷን መሰለች ጠቅሟታል። አቶ ዘለቀ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህር ናቸው። ታዲያም ትምህርት ቤት ወስደው የስምንተኛ ክፍል ትምህርቷን ለመቀጠል ሊያስመዘግቧት ሞከሩ። ሆኖም ምዝገባው አልፎ ስለነበር ሳትመዘገብ ቀረች። ይሄ የሆነው እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2019 ነበር።

በዓመቱ ማለትም በፈረንጆቹ 2020 መሰለች ቀድሞ ትማርበት የነበረው ጆርጊ ትምህርት ቤት ከስምንተኛ ክፍል ያቋረጠችውን ትምህርቷን ለመቀጠል ተመዘገበች። መሰለች ትምህርቷን የቀጠለችው የዓይን ብርሃኗን በማጣቷ አንብባ፣ተረድታና ጽፋ ፈተናውን መሥራት የሚያስችላትን የብሬል ትምህርት ጎን ለጎን በመማር ነበር። በዚህ ሁኔታ ተምሮ ፈተና መፈተኑ እጅግ ቢከብድም መሰለች ተያያዘችው።



ተማሪ መሰለች ጃናቶ፣

‹‹የብሬል ትምህርት በአካታችነት ይሰጥበት የነበረው ሙዳላ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሳምንት ሁለት ቀን እየሄድኩ የብሬል ትምህርት አከታተል የነበረ መሆኑ የበለጠ አድካሚ ነበር›› ስትል ታወሳዋለች።

እሷ እንደምትለው ሆኖም የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር አቶ አበጆ አቺኮ በጥናትም በማበረታታትም ይረዷት ነበር። የልዩ ፍላጎት መምህሯ ታገሰች በብሬል ልምምዱ ወቅት ከፍተኛ እገዛ አድርጋላታለች። እናም በዚሁ ዓመት የስምንተኛ ክፍል ፈተና ተፈተነች።ጥሩ ውጤትም ማምጣት ቻለች።

‹‹በፈተናው አጥጋቢ ውጤት ማምጣት የቻልኩትም ብሬል በመከታተሌና እነዚህ ሰዎች ያግዙኝ ስለነበረ ነው›› ብላናለች።የብሬል ትምህርት እንድትከታተል ያደረጋት WEEMA International የተባለ ድርጅት እንደሆነ የምታወሳው መሰለች ‹‹ድርጅቱ እየተመራሁ ትምህርት ቤት እሄድበት የነበረውን በትር(ዘንግ) ጨምሮ የድምፅ መቅጃ ሪከርደር፣ ለሪከርደሩ የሚውሉ ባትሪ ድንጋዮች፣ የብሬል ስቴንስሎች፣የብሬል ወረቀቶችን ድጋፍ አድርጎልኛል››የምትለው መሰለች ድርጅቱ እና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ያደርግላት የነበረው ድጋፍ ተስፋዋን ሁሉ እንደገና እንደመለሰላት ታወሳለች። በተለይ ድርጅቱ ትምህርት እንደጀመረች ከትምህርት ሰዓት ውጪ በተከታታይ በስነ ልቦና ባለሙያዎች የምክር አገልግሎት እንድትወስድ ያደረግላት የነበረ መሆኑን ታስታውሳለች።

‹‹ይሄን አገልግሎት ማግኘቴ ከእንግዲህ ዋጋ የለኝም ብዬ በተደጋጋሚ ረሳሴን ለማጥፋት አደርጋቸው የነበሩት ሙከራዎች ትክክል እንዳልነበሩ ዞር ብዬ ወደ ውስጤ እንዳይ አድርጎኛል።በራሴ እንድተማመንና ብሬል ተምሬ ትምህርቴን መከታተል ብሎም እንደ ዓይናማነቴ ዘመን ሁሉ ጥሩ ውጤት ማምጣት እንደምችል የሚያደርግ ጥሩ ግንዛቤ ፈጥሮልኛል ››ትላለች መሰለች።እንድትበረታታና ተስፋ እንዲኖራትም አስችሏታል።

መሰለች ስምንተኛ ክፍል ፈተናን በአጥጋቢ ውጤት በማለፏ ሆዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ሆና ገባች። ሆዶ ትምህርት ቤት በፊት እንደምትማርበት ትምህርት ቤት ሁሉ የትምህርቱ ማህበረሰብ መምህራን ተማሪዎች ያበረታቷትና ድጋፍ ያደርጉላት ነበር። WEEMA International የተባለው ድርጅት ምክርና የትምህርት አጋዥ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ድጋፍ አልተለያትም። የሚያስፈልጋትን ሁሉ በማቅረብ ከጎኗ ነበር። በመሆኑም በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ ከሁሉም የደረጃ ተማሪዎች አንዷ በመሆን ተሸለመች። ጥሩ ውጤት በማምጣትም ወደ 10ኛ ክፍል ተዛወረች።

‹‹አሁን ሕይወት ለኔ አጓጊ ሆናልኛለች። ትልቅ ደረጃ የመድረስና በትምህርቴ ፕሮፌሰር እስከመሆን የሚያስችል ተስፋ ሰንቂያለሁ››ትላለች መሰለች ሀሳቧን ስትቋጭ። እኛም ተስፋዋ ዕውን እንዲሆን የሁሉም ድጋፍ አይለያት በማለት ጽሑፋችንን ደመደምን።

# ዓለም አቀፍ

## በአሸናፊነት ስሜት 18 ሺህ ቲሸርቶችን ያሳተመው እንግሊዛዊ ኪሳራ ገጥሞታል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አገሬ የዓለም ዋንጫ ታሸንፋለች በማለት በራሱ ወጪ 18 ሺህ ቲሸርቶችን ያሳተመው እንግሊዛዊው የእግር ኳስ አፍቃሪ ካርል ባክስተር ለኪሳራ መዳረጉ ቢቢሲ አስነበበ።

ካርል ባክስተር አገሩ በኳታር እንደምትነግስ ምንም አይነት ጥርጣሬ እንዳልነበረውና ሶስቱ አናብስት የዓለም ዋንጫውን ከዶሃ ወደ ለንደን ይዘው እንደሚመለሱም ሙሉ እምነት እንደነበረውም ተገልጿል።

ከሩብ ፍጻሜ ጨዋታዎች አስቀድሞም “እንግሊዝ የ2022 የዓለም ዋንጫ ሻምፒዮን በመጨረሻም ዋንጫው ቤታችን ገብቷል” የሚል ጽሁፍ ያለባቸውን 18 ሺህ ቲሸርቶች አትሞ የሚያገኘውን ትርፍ ማስላት መጀመሩም ተነግሯል።




ነገር ግን እንግሊዝ በሩብ ፍጻሜው ፍልሚያ በፈረንሳይ 2 ለ 1 ተረታ ከዶሃ የተሰናበተች ሲሆን በ1966 በዌንብሌይ ስታዲየም ራሷ ያዘጋጀችውን የዓለም ዋንጫ ካነሳች በኋላ የዓለም ዋንጫው እንደናፈቃት የቀረችው እንግሊዝ ግን እንኳን ዋንጫውን ልታነሳ ለግማሽ ፍጻሜው አልደረሰችም።

ይህን ጨዋታ ከየትኛውም እንግሊዛዊ በተለየ ስሜት የተከታተለው ባክስተር ሃዘኑ ተደራርቦበታል።

“ለዓመታት ምንም አይነት ጽሁፍ የሌላቸውን ቲሸርቶች ገዝተን ምንም አልተፈጠረም (ዋንጫ ወስደን ያሻንን አልጻፍንባቸውም)፣ እናም ድልን የሚተነብይ ጽሁፍ ያላቸው ቲሸርቶች አሳተምኩ” ይላል የ46 አመቱ ባክስተር።

ሶስቱ አናብስት ባሳዩት ብቃት እንደሚኮራ የሚያነሳው ነጋዴው ባክስተር ፥ ለእንግሊዛውያን መልዕክት አለው፤ የታተሙትን 18 ቲሸርቶች ግዙኝና ከኪሳራ ታደጉኝ የሚል ጥሪም አቅርቧል።

“የቲሸርቶቹን ዋጋ ቀንሰናል፤ በኩራት ልበሷቸው፣ ለታሪክ በክብር አስቀምጧቸው፣ የመስኮት መወልወያም ልታደርጓቸው ትችላላችሁ፣ አላውቅም” የሚል የግዙኝ ተማጽኖውንም በድረ ገጹ ላይ አስፍሯል።

ሆኖም ግን የሶስት ልጆች አባቱ የእግር ኳስ አፍቃሪ ነጋዴው ባክስተር ለቲሸርቶቹ ዝግጅት ያወጣው ወጪ የተጋነነ አይደለም፥ የተወሰኑትንም ሸጧል ተብሏል።

እንግሊዝ በወንዶቹ ባይሳካላትም በሴቶቹ የ2022 የአውሮፓ ዋንጫን ስላነሳች የቲሸርቱን ሽያጭ ወዳዚያው የማዞር አማራጭም ይዟል።

29 ነጥብ 99 ፓውንድ ስተርሊንግ ሊሸጥ የነበረው ነጭ ቲሸርት አሁን የ9 ነጥብ 99 ፓውንድ ዋጋ ወጥቶለታል ተብሏል

## በኮንጎ ከ120 በላይ ሰዎች በጎርፍ አደጋ ሕይወታቸውን አጡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በዓመታት ውስጥ ከታዩት ሁሉ የከፋው ነው የተባለ የጎርፍ አደጋ በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ መዲና ኪንሻሳ ውስጥ ከ120 በላይ ሰዎችን መግደሉን ቢቢሲ ዘገበ።

ከባድ ዝናብ ለሰዓታት ከዘነበ በኋላ የከተማዋ ዋና አውራ ጎዳኖች በውሃ ሲዋጡ፣ መኖሪያ ቤቶች ደግሞ በጎርፍ ተወስደዋል። እንደ የአገሪቱ ባለሥልጣናት ከሆነ አብዛኛው ሟቾች በተራራማ ቦታ ይኖሩ የነበሩ እና በመሬት መንሸራተት ምክንያት ሕይወታቸውን ያጡ ናቸው።

በጎርፉ አደጋ ከሞቱት በርካታ ሰዎች ከአንድ ቤተሰብ ዘጠኝ ሰዎች መሞታቸው አደጋውን አስከፊ እንደሚያደርግና የአገሪቱ መንግሥት ለሦስት ቀናት የሚዘልቅ ብሔራዊ የሐዘን ጊዜ ማወጁ ተነግሯል።

ጉዳቱ ባጋጠመበት ቦታ ነዋሪ የሆኑት በላንቻርድ ቩቡ “በዚህ ደረጃ ጎርፍ አይተን አናውቅም” ብለዋል። “ተኝቼ ነበር። ጎርፍ ቤት ውስጥ ሲገባ ታወቀኝ። ከባድ ውድመት ነው። ሁሉም ንብረታችንን አጥተናል። ቤታችን እና ምንም ንብረት አልተረፈንም” ብሏል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጄን-ሚቼል ሳማ ሉኮንዴ አስተዳደር ልዑካን ያጋጠመውን ጉዳት ለመመልከት ወደ ኪንሻሳ አካባቢዎች ማቅናታቸውና የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በአደጋው ሳይሞቱ አይቀርም የተባሉ የተጨማሪ ሰዎች አስከሬን እየተፈለገ መሆኑ ተጠቅሷል።

ቀደም ሲል የአገሪቱ ፕሬዝዳንት ለደረሰው ጉዳት የአየር ለውጥ ምክንያት ነው ሲሉ ተናግረው ነበር። “ዴሞክራቲክ ኮንጎ ጫና ውስጥ ናት ይሁን እንጂ በአግባቡ አልተደገፈችም ወይም አልተደመጠችም” ሲሉ ለአሜሪካ-አፍሪካ የመሪዎች ስብሰባ ዋሽንግተን የሚገኙት ፕሬዝዳንት ፌሊክስ ቲሺሴኬዲ ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ኃላፊ አንቶኒ ብሊንከን ተናግረዋል።

የፕሬዝዳንቱ ቃል አቀባይ ቲሺሴኬዲ የዋሽንግተን



ዲሲ ቆይታቸውን በማሳጠር ወደ አገራቸው ሊመለሱ ይችላሉ ብለዋል። በአፍሪካ አሜሪካ ጉባኤ ላይ እየተሳተፉ የሚገኙት የዲሞክራቲክ ኮንጎ ፕሬዝዳንት፣ ከአሜሪካው አቻቸው ጋር ከተነጋገሩ በኋላ በአደጋው ምክንያት ሐሙስ ዕለት ወደ አገራቸው እንደሚመለሱ በትዊተር ገጻቸው ላይ አስፍረዋል።

በኮንጎ ወንዝ ዳርቻ የምትገኘው ኪንሻሳ በቅርብ ዓመታት ውስጥ የነዋሪዋ ቁጥር በከፍተኛ መጠን የጨመረ ሲሆን አሁን ላይ ከ15 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ እየኖረ ይገኛል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን

የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፦ www.press.et
ፌስቡክ፦ Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ሐሙስ ስፖርት



ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!



በጠረጴዛ ቴኒስ፣ በፑል፣ በከረንቡላ፣ በቼዝ፣ በዳርት፣ በዳማ እና በጆተኒ ጨዋታዎች በሰራተኞች መካከል ውድድር እየተካሄደ ነው፣

## «ስፖርት ለሁሉም» የሰራተኞች ውድድር ተጀመረ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የ2015 ዓ.ም የሰራተኞች ስፖርታዊ ውድድርና ጨዋታ ‹‹ስፖርት ለሁሉም›› በሚል መሪ ቃል በቢሮው የሰራተኞች መዝናኛና ጅምናዚየም ማዕከል ትናንት በድምቀት ተጀምሯል።

ውድድሩን ያስጀመሩት የቢሮው አማካሪ አቶ በኃይሉ በቀለ፣ ሰራተኞች በተለያዩ ስፖርቶች ላይ በመሳተፍ እየተዝናኑ የሚያስመዘግቡት ውጤት መነቃቃትን እንዲፈጥርላቸው ተናግረዋል።

‹‹ውድድሩ የሰራተኞችን ግንኙነት ያጠናክራል›› ያሉት አቶ በኃይሉ በስፖርት የዳበረ ሰራተኛ ጤናውን ከመጠበቁ ባሻገር አገልግሎት አሰጣጡንም ውጤታማ ያደርገዋል ብለዋል።

የ2015 የሰራተኞች መዝናኛ ጨዋታ ተወዳዳሪዎችን እና ደጋፊዎችን ከማዝናናት ባለፈ ጤናማ ሲቪል ሰርቫንት ለመፍጠር እንደሚያስችል የገለፁት የማሕበረሰብ ስፖርት ማስፋፊያና ተሳትፎ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ እንግዳወርቅ ዳንኤል በዘንድሮ ጨዋታ በጠረጴዛ ቴኒስ፣ በፑል፣ በከረንቡላ፣ በቼዝ፣ በዳርት፣ በዳማ እና በጆተኒ ጨዋታዎች በሰራተኞች መካከል ውድድር እንደሚደረግ አስታውቀዋል።

ውድድሮቹ በሁለቱም ጾታ እንደሚደረግ የገለጹት አቶ እንግዳወርቅ፣ ተወዳዳሪዎች የወጣውን መርሃ ግብር በማየት በውድድሩ ቦታ እና ሰዓት እንዲገኙ አሳስበዋል።

የ2015 ዓ.ም የሰራተኞች ጨዋታ ውድድር ላይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ቢሮ፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የሚሳተፉ ሲሆን ከታሕሳስ 5 እስከ 25 2015 ዓ.ም የሚቆይ ይሆናል።

## ዓለም ዋንጫ የጋረደው ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪምየርሊግ

ዓለምአየሁ ግዛው

ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪምየርሊግ ሁለተኛ ዙር ፉክክር ሊቋጭ የሁለት ጨዋታ ዕድሜ ብቻ ቀርቶታል። ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ባህርዳር ከተማ እና ኢትዮጵያ መድን በተቀራራቢ ነጥብ በደረጃ ሰንጠረዡ ፉክክር ያደመቁት ሊጉ የድሬዳዋ ቆይታ በምን መልኩ እንደሚጠናቀቅ በጉጉት ይጠበቃል። የሊጉን የደረጃ ሰንጠረዥ እየተቀያየሩ ከሚመሩት ሦስቱ ክለቦች በተጨማሪ በወራጅ ቀጠናው ሲዳማ ቡና፣ ኢትዮ ኤሌትሪክ እና ለገጣፎ ለገዳዲ የሚያደርጉት ትግልም በሊጉ የድሬዳዋ ቆይታ ትኩረት የሳበ ጉዳይ ነው። የከፍተኛ ግብ አግቢነቱ ፉክክር በቶጎዋዊው የፈረሰኞቹ ግብ አምራች እስማኤል ኦሮ አጎሮ አስር ግቦች እየተመራ ቢገኝም፤ ጌታነህ ከበደ ከወልቂጤ ከተማ በተመሳሳይ አስር ግቦች አስቆጥሮ ፉክክሩን አጓጊ አድርጎታል። የባህርዳር ከተማው ፍጹም ዓለሙም በሰባት ግቦች የኮከብ ግብ አግቢነቱን ፉክክር በቅርብ ርቀት እየተከተለ ይገኛል።

በሊጉ እየተሳተፉ የሚገኙ ክለቦች ከውጤት ማጣት ጋር ተያይዞ የአሰልጣኞችን ስንብት ያስታወቁበት ያለፉት ሳምንታት አነጋጋሪ ጉዳዮች ነበሩት። አንዳንድ ክለቦች ለተጫዋቾች ደሞዝ መክፈል አለመቻልም ሊጉ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ያስተናገዳቸው አበይት ክስተቶች ናቸው። በኳታሩ የ2022 ዓለም ዋንጫ ምክንያት የሊጉ ያለፉ ጥቂት ሳምንታት ጨዋታዎች የቀጥታ ቴሌቪዥን ስርጭት ማጣት ውስጥ ቢከርሙም ፉክክሩ ግን ተጠናክሮ ቀጥሏል። የአሰልጣኝ ስንብት ካደረጉ ክለቦች መካከል ለገጣፎ ለገዳዲ በቅርብ የሚጠቀስ ነው። ለገጣፎ ለገዳዲ የቀድሞ አሰልጣኙን ወደ ምክትል አሰልጣኝነት በማውረድ





አሸናፊ በቀለን በዋና አሰልጣኝነት ከቀናት በፊት እንደሾመ ይታወሳል።

የሊጉ የመጀመሪያ ዙር ጨዋታዎች ባህርዳር ላይ ሲካሄዱ ከሱፐር ስፖርት ቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት ጋር በተያያዘ ትልቅ ትኩረት አግኝቶ የነበረው ቢሆንም በሁለተኛው ዙር የድሬዳዋ ቆይታው በዓለም ዋንጫ ምክንያት ሊቋረጥ ችሏል። ከተለመደው ሰኔ ወደ ህዳር ቀይሮ እየተካሄደ የሚገኘው ትልቁ የዓለም ዋንጫ በሌሎች አገራት ሊጎች ላይ የፈጠረው ተፅዖኖ ተመሳሳይ ባይሆንም በኢትዮጵያ ፕሪሚየርሊግ ላይም አርፏል። ቢያንስ ሊጉ ከቴሌቪዥን ስርጭት ጋር በተያያዘ ሽፋኑን ማግኘት ያልቻለ ሲሆን ይህም ከድሬዳዋ ውጪ ያለው ተመልካች በቅርበት እንዳይከታተለው ሆኗል።

ፕሪምየር ሊጉ የስያሜ መብቱን ከሸጠ፣ የሱፐር ስፖርት ቀጥታ ቴሌቪዥን ሽፋኑን ካገኘና በሼር ካምፓኒ መተዳደር ከጀመረ ወዲህ የአገር ውስጥ ተመልካች ትኩረትን መሳቡ እርግጥ ነው።

## ለ2ኛ ጊዜ የወጣ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር ግዥ/ን /394/2015ዓ.ም

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ ገ/ጽ/ቤት ግዥ ለሚፈፅምላቸው ሴክተር መ/ቤቶች በመደበኛ በጀት ሎት 1 ፣ ኤሌክትሮኒክስ ሎት 2 ቋሚ እቃ ሎት 3 ፈርኒቸርና የግንባታ እቃ በአልማ በጀት አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል። ስለዚህ በዘርፉ ንግድ ፈቃድ ያለው ማንኛውም ተጫራች የሚከተሉትን መስፈርቶች በማሟላት መወዳደር ይችላል::

1. በዘመኑ የታደሰ ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው
2. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ያላቸው
3. የግዥ መጠኑ ከ200,000 / ሁለት መቶ ሺህ ብር / በላይ ከሆነ የቫት ተመዝጋቢ መሆን አለበት
4. ተጫራቾች በጨረታ ለመሳተፍ ከላይ የተጠቀሱትን እና የሚመለከታቸውን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፣
5. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ወይም ቢን ቦድ እስከ 60/ ስልሳ /ቀን ያላነሰ የሆነ ለሚወዳደሩበት የእቃው ጠቅላላ ዋጋ 2% በጥሬ ገንዘብ / ሲፒኦ/ ማስያዝ የሚችሉ መሆን አለባቸው
6. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሃሳቡን አንድ ወጥ በሆነ በጥንቃቄ በታሸገ ፖስታ በለጋምቦ ወረዳ ገ/ጽ/ቤት በግዥ ቡድን ወይም በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 16ኛው ቀን 4፡00 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል::
7. ሁሉም ውድድሩ የሚካሄደው በየሎቱ በድምር አሸናፊ ይሆናል::
8. የጨረታው መከፈቻ ቀን ቅዳሜ እና እሁድ እንዲሁም የበአል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰአት ይሆናል።
9. ጨረታው ጋዜጣው ከወጣበት 16ኛው ቀን 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በ4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙት ይከፈታል።
10. መ/ቤቱ በእያንዳንዱ ግዥ ላይ 20% የመጨመርና የመቀነስ መብቱ የተጠበቀ ነው፣
11. የጨረታ ሰነዱ ስርዝ ድልዝ ካለው ከጨረታ ውጭ ይሆናል፣
12. አሸናፊው ድርጅት እቃውን የሚያስረክበው በወረዳው ውስጥ ባሉ ሴክተር መ/ቤት ነው።
13. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ስለ ጨረታው ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ ቢሮ ቁጥር 2 ድረስ በአካል በመገኘት ወይም በስልክ ቁጥራችን 033 114 01 05 በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ::
14. ተጫራቾች በፖስታው ላይ ቀን ስም፣ ፊርማ እና ስልክ ቁጥር የሚወዳደሩበትን ዘርፍ መጻፍ ይኖርባቸዋል።
15. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልግ የጨረታ ሰነድ የማይመለስ 100/ አንድ መቶ ብር/ በመክፈል ለጋምቦ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 2 በመምጣት መግዛት የሚቻል መሆኑን እንገልጻለን።
16. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

**በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ ገ/ጽ/ቤት**

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | |
|---|---|
| 1. ስም:- ሸንዘን ቲሰንክ ሜዲካል ዲቫይስስ ኮ ኤልቲዲ (Shenzhen Tisenc Medical Devices Co., Ltd.) **አድራሻ:-** 11F, 11G, Kechuang Building, Quanzhi Science and Innovation Park, Maozhoushan Industrial Park, Houting Community, ShaJing Street, BaoAn District, ShenZhen, 518104, People's Republic of China | |
| 2. ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን | 04/11/2022 እ.ኤ.አ |
| 3. የማመልከቻ ቁጥር | FTM/13850/22 |
| 4. የንግድ ምልክቱ መግለጫ | የቃል እና ምስል |
| 5. የንግድ ምልክቱ | TiSENC |
| 6. አለም አቀፍ ምድብ | 05 እና 10 |

ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች

**ምድብ 05፡** ለህክምና ወይም ቬተርነሪ አገልግሎት የሚሆኑ ኬሚካል ሪኤጀንቶች ለህክምና አገልግሎት የሚሆኑ ዲያግኖስቲክ ባዮማርከር ሪኤጀንቶች፤ ለህክምና አገልግሎት የሚሆኑ ኢሚኖአሳይ ሪኤጀንቶች፤ ለህክምና አገልግሎት የሚሆኑ ሪኤጀንቶች ለህክምና አገልግሎት የሚሆኑ ዲያግኖስቲክ ሪኤጀንቶች፤ ለህክምና የዘረ-መል ምርመራ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሪኤጀንቶች ለህክምና አገልግሎት የሚሆኑ ዲያግኖስቲክ ዝግጅቶች ለህክምና እና ቬተርነሪ አገልግሎት የሚውሉ ዲያግኖስቲክ ዝግጅቶች ለህክምና ወይም ቬተርነሪ አገልግሎት የሚውሉ ዲያግኖስቲክ ዝግጅቶች ለቬተርነሪ አገልግሎት የሚውሉ ዲያግኖስቲክ ዝግጅቶች

**ምድብ 10፡-** ለቬተርነሪ አገልግሎት የሚውሉ የቀዶ ጥገና አፓራተስ እና መሳሪያዎች የቬተርነሪ አፓራተስ እና መሳሪያዎች የህክምና አፓራተስ እና መሳሪያዎች በህክምና ትንተና ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል አፓራተስ፤ ለህክምና አገልግሎት የሚውል የመመርመሪያ አፓራተስ ለህክምና አገልግሎት የሚውል ዲያግኖስቲክ አፓራተስ፤ ለህክምና አገልግሎት የሚውል የዘረ-መል መመርመርያ አፓራተስ፤ ለህክምና አገልግሎት የሚውል የዲኤንኤ እና አርኤንኤ መመርመርያ አፓራተስ፤ የሰውነት ውህድ ሞኒተሮች የህክምና ናሙና መቀበያ ካፖች ናቸው::

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል። ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ ይህ የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰውን የንግድ ምልክት በምዝገባ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ካልቀረበ በስተቀር ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናሳውቃለን።

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**
**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXII No-096 06/04/2015 (15/12/2022)**